# ህግህ ለእግሬ መብራት

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት - ዘዳግም

አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት



ክፍል አንድ

ከአድንሙ ተሻሽሎ 1993 ዓ.ም

# ሕግህ ለእግሬ መብራት

ከአድነው ተሾመ

1993 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)

## ክፍል አንድ

ይህንን መጽሐፍ ያ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ
ወይም በከፊል ማባዛት ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው 1993 ዓ.ም

**Copyright 2001, Adnew Teshome**

# ምዕራፍ አምስት

## ዘኍልቍ

(ዘኍልቍ) ማለት «የቁጥር» ማለት ሲሆን፣ ይህ መጽሐፍ ይህንን ስም ያገኘበት ምክንያት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ ሁለት ጊዜ ስለተቆጠረ ነው። በመጀመሪያ ከግብጽ የወጣው ትውልድ ተቆጠረ። በሁለተኛው ጊዜ አዲሱ ትውልድ ተቆጠረ።

ይህንንም መጽሐፍ ሙሴ እንደጻፈው ይታመናል።

የዘኍልቍ መጽሐፍ ከዘጸአት መጽሐፍ መጨረሻ የሚቀጥል ታሪክ ቢሆንም የዘሌዋውያንን መጽሐፍ በመካከል እናገኛለን።

በዘጸአት መጨረሻ እንዲህ ይላል፣ «እንዲህም ሆነ በሁለተኛው ዓመት በፊተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ማደሪያው ተተከለ።» ዘጸ.40፡17

በዘኍልቍ መጀመሪያ ደግሞ እንዲህ ይላል« እግዚአብሔርም ሙሴን በሲና ምድረ በዳ በመገናኛው ድንኳን ወስጥ በሁለተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ከግብጽ ምድር ከወጡ በኋላ በሁለተኛው ዓመት እንዲህ ብሎ ተናገረው»(ዘኍ.1፡1)።

ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች እንደምናየው በዘጸአት መጨረሻና በዘኍልቍ መጀመሪያ መካከል የአንድ ወር ልዩነት ብቻ ነው ያለው።

የዘኍልቍ መጽሐፍ ከሁለተኛው ዓመት ሁለተኛ ወር ጀምሮ እስከ አርባኛው ዓመት አሥራ አንደኛው ወር ይደርሳል(ዘዳ.1፡3) በአጠቃላይ የዘኍልቍ መጽሐፍ የእስራኤላውያንን በምድር በዳ መቅበዝበዝና ከግብጽ የወጣው ትውልድ በሙሉ እንዳለቀ የሚተርክ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ የ38 ዓመታት የምድረ በዳ ታሪክ ያዘለ ነው ማለት እንችላለን።

<u>ይህ መጽሐፍ ሁለት ትውልዶችን ያጠቃልላል።</u>

1. ከግብጽ የወጣውና በምድረ በዳ ያለቀው ትውልድ (ምዕ. 1-14)
2. በምድረ በዳው አደጉ ወደ ከነዓን የገባው ትወልድ (ምዕ. 21-36)::

በሁለቱ ትውልዶች ታሪክ መካከል ከግብጽ የወጣው ትውልድ ያለቀበትና አዲሱ ትውልድ የተተካበት የምድረ በዳ ጉዞ አለ (ከምዕ 15-20)

<u>መጽሐፉ በአጠቃላይ በሦስት ይከፈላል፤</u>

1. ከግብጽ ስለወጣው(በምድረ በዳ ያለቀው) ትውልድ ከሲና እስከ ቃዴስ በርኔ (ምዕ. 1-14)
2. የምድረ በዳው መቅበዝበዝ (ምዕ. 15-20)
3. አዲሱ( ወደ ከነዓን የገባው) ትውልድ
ከቃዴስ በርኔ እስከ ከነአን ድንበር (ምዕ. 21-36)

እነዚህን ክፍሎች በምናይበት ጊዜ የምድረ በዳው መቅበዝበዝ (ከምዕ. 15-20) የ38 ዓመታት ዘመን (ዘዳ. 2፤14-15) ሲሆን የተካተተው ግን በ6 ምዕራፎች ብቻ ነው:: ነገር ግን ሌሎቹ ክፍሎች የጥቂት ወራት ርዝመት ቢኖራቸውም እነርሱን ለመተረክ 30 ምዕራፎች ፈጅቷል:: ከዚህ የምናስተውለው እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጠው የዘመናት ርዝመት ላይ ሳይሆን በድርጊቶቹ ቁም ነገረኛነትና ትምህርታዊ ይዘት ላይ ነው::

<u>የዘኍልቁ መጽሐፍ መልእክት: -</u>

ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን <u>ቸርነት (ምህረት) እና ፍርድ</u> የሚያሳይ ነው:: በአንድ በኩል እግዚአብሔር ለ40 ዓመታት ያህል እስራኤላውያንን እንዴት እንደተንከባከባቸው ሲያሳይ÷ በአንጻሩ ደግሞ እነርሱ ምን ያህል በየጊዜው ያጉረመርሙና ያምጹ እንደነበር፤ በአመጻቸውም ምክንያት እግዚአብሔር በተለያዩ መቅሠፍቶች እንደመታቸው የሚገልጽ መጽሐፍ ነው:: «እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት» (ሮሜ 11÷22) የሚለው ጥቅስ ይህንን መጽሐፍ ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል::
<u>በአዲስ ኪዳን ከዚህ መጽሐፍ እንድንማር የሚያሳስቡ ክፍሎች</u>: -

1ኛ ቆሮ. 10÷1-12
ቁ 6 «ክፉ ነገር እንደተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ»

ቁ. 8 «አንዳንዶቹ እንደሴሰኑ አንሴስን።»
ቁ. 9 «እንደተፈታተኑት አንፈታተን»
ቁ. 10 «አንዳንዶች እንዳንጎራጎሩ አታንጎራጉሩ»

እነርሱ እንዳደረጉት አታድርጉ ብቻ ሳይሆን፣ እነርሱ ላደረጉት ነገር ቅጣታቸውን እንደተቀበሉም ያሳስበናል።

- ክፉ የተመኙት በመቅሰፍት ተመቱ (ዘኍ. 11÷33)
- የሴሰኑት ወደቁ (ሞተ) (1ኛ ቆሮ. 10÷8)
- ያጉረመረሙት በሚያጠፋው ጠፉ (1ኛ ቆሮ. 10÷10)

በዕብ. 3÷7-19 ደግሞ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል። «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ አባቶቻችሁ እኔን የፈተኑበት የመረመሩበትም አርባ ዓመትም ሥራዬን ያዩበት በምድረ በዳ በፈተና ቀን በማስመረር እንደሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ... ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉ የማያምን ልብ እንዳይኖር ተጠንቀቁ... ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ ... ካልታዘዙትም በቀር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? ባለማመናቸው ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን።»
ይህ ክፍል የሚያስጠነቅቀን፡ -

- ልባችንን እልከኛ እንዳናደርግ (ቁ. 8-9፣15)
- ከክፉና ከማያምን ልብ እንድንጠነቀቅ( 12፣19)
- ከአለመታዘዝ እንድንጠነቀቅ( ቁ. 18)

## <u>ክፍል 1 - የቀድሞው ትውልድ</u> (<u> ምዕ. 1-14</u>)

ይህ ክፍል ከሲና እስከ ቃዴስ በርኔ (ሰላዮች ከነዓንን እንዲሰልሉ የተላኩበት ቦታ) ባለው ታሪክና ጉዞ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ ክፍሉ <u>በሦስት</u> ይከፈላል፤

ሀ. የሕዝብ ቈጠራ (ከምዕ. 1-4)
ለ. የተሰጡ ትእዛዛት(ከምዕ. 5 -ምዕ. 10፡ 10)
ሐ. ጉዞ (ምዕ. 10፣11-ምዕ. 14)

ሀ. *የሕዝብ ቆጠራ*: -(ምዕ.1-4)

የዚህ የሕዝብ ቆጠራ ዓላማ «ለሰልፉ ማዘጋጀት» እንደነበረ እናነባለን፡፡ የተቆጠሩት ወንዶች ብቻ ነበሩ፡፡ «ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለውን ከእስራኤል ወደ ሰልፉ የሚወጡትን ሁሉ አንተና አሮን በየሠራዊታቶቻቸው ቁጠሩአቸው»( ምዕ. 1፡3)፡፡

የሌዋውያን ነገድ በዚህ የሰልፍ ቆጠራ ውስጥ እንዳልነበሩ እናያለን፡፡ የእግዚአብሔርን ድንኳን የሚያገለግሉ ነበሩ፡፡ «የሌዊን ነገድ አትቁጠረው ቁጥራቸውንም ከእስራኤል ልጆች ጋር አታድርግ ... «ማደሪያዎችንና ዕቃዎችን ሁሉ ይሸከሙ» (ምዕ. 1፥49-51)፡፡

በሌዊ ነገድ ፋንታ የዮሴፍ ሁለት ልጆች ምናሴና ኤፍሬም እንደ ሁለት ነገድ ስለተቆጠሩ በአጠቃላይ 12 ነገዶች ሆነው ነበር የተቆጠሩት፡፡

የእነዚህ 12 ነገዶች አቀማመጥ ሦስት ሦስት ነገዶች ሆነው በአራቱ አቅጣጫ በመገናኛው ድንኳን ዙሪያ ነበር፡፡




ይህ አሰፋፈር ራሱ፤ እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ እንደሆነ ያሳያል፡፡
እግዚአብሔር በማደሪያው ድንኳን በመካከላቸው ነበረ (ዘኊ. 5፥3)

የሦስቱ የሌዊ ልጆች፤ ማለትም የጌድሶን፣ የቀዓትና የሜራሪ ትውልዶች ደግሞ በመገናኛው በምዕራብ፣ በደቡብና፣ በሰሜን አቅጣጫ ይሰፍሩ ነበረ። በመጨረሻም፣ ሙሴ፣ አሮንና ልጆቹ በመገናኛው ፊት በምሥራቅ በኩል ይሰፍሩ ነበረ።

በምዕ. 1 የምናየው ፡ - የ12ቱ ነገዶች (ከሌዊ በቀር) ቆጠራ ነው። የተቆጠሩት ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ለሰልፍ የሚወጡ ነበሩ። የእነዚህ አጠቃላይ ቁጥር፡ - 603,550 ነበረ (ምዕ. 1፥46)።

ምዕ.2 የእነዚህን 12 ነገዶች አሰፋፈር ያሳያል፤ በሥዕሉ እንደሚታየው ማን በሰሜን፣ በደቡብ በምሥራቅና በምዕራብ እንደሚሰፍር ይገልጻል።

በምዕ. 3 የሌዊ ነገድ ቆጠራ ተገልጾአል። የእግዚአብሔር «በእስራኤል ልጆች ዘንድ ማኅፀን የሚከፍተው ሁሉ የእኔ ነው።» ባለው ፊንታ «የሌዊን ነገድ መርጫለሁ» በማለት የሌዊን ነገድ ለራሱ ይለያል( ምዕ. 3፥11-13 )የሌዊ ነገድ የተቆጠሩት እንደሌሎቹ ነገዶች ከ20 ዓመት ጀምሮ ሳይሆን ከአንድ ወር ጀምሮ ነበረ። «ወንዱን ሁሉ ከአንድ ወር ጀምሮ ከዚያም በላይ ያለውን ቁጠራቸው( ምዕ. 3፥15)። የሦስቱ የሌዊ ልጆች ትውልድ አጠቃላይ ድምር 22,000 ነበረ( ምዕ. 3፣39)። እነዚህም በእስራኤላዊያን በኲሮች ፊንታ ለእግዚአብሔር የተለዩ ነበሩ።

በምዕ. 4 የሦስቱ የሌዊ ልጆች ወገኖች የተሰጣቸውን የአገልግሎት ድርሻ ያሳያል። ሁሉም በተሰጠው አገልግሎት ብቻ መሰለፍ ነበረበት።

ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ብቁ የነበሩት ከሠላሳ ዓመት እስከ ሃምሳ ዓመት ድረስ የነበሩት ብቻ ነበሩ፤ «ከሠላሳ ዓመት ጀምሮ እስከ ሃምሳ ዓመት ድረስ በመገናኛው ድንኳን ይሠሩ ዘንድ ለአገልግሎት የሚገቡትን ሁሉ ትደምራለህ»( ቁ. 3፣ 23፣30)።

<u>የመገናኛው ድንኳን በሚተከልበትና በሚነቀልበት ጊዜ፡ -</u>

*የቀዓት ልጆች ሥራ፡* - በመገናኛው ድንኳን <u>ውስጥ ያሉትን</u> ዕቃዎች መሸከም (ምዕ. 1፥5-15)።

*የጌድሶን ልጆች ሥራ* ፡ - ከጎንና ከላይ ያሉትን መጋረጃዎች መሸከም (ምዕ. 1፥24-26)።

የሜራሪ ልጆች ሥራ፡ - የድንኳኑን ምሰሶዎች ሳንቃዎች፣ ካስማዎች መወርወሪያዎች...በአጠቃላይ መዋቅሩን መሸከም (ምዕ. 1÷31-32)።

አሮንና ልጆቹ (አልዓዛርና ኢታምር) የራሳቸው የሆነ የማስተባበር ኃላፊነት ነበራቸው።

ቁ. 19ለ፡ - «... አሮንና ልጆቹ ይግቡ ለሰውም ሁሉ ሥራውንና ሸክሙን ይዘዙ።»

ቁ. 16 «የካህኑም የአሮን ልጅ አልአዛር በመብራት ዘይት በጣፋጩም ዕጣን ላይ ሁልጊዜም በሚቀርበው በእህሉ ቁርባንና በቅባቱ ዘይት ላይ ይሾም፣ ማደርያውን ሁሉ በእርሱም ውስጥ ያለውን ሁሉ መቅደሱንና ዕቃውን ይጠብቃል።»

የጌድሶናውያንና የሜራሪ ልጆች ኃላፊነት ከአሮን ልጅ ከኢታምር በታች ነበር( ቁ. 28 እና 33)።

የእነዚህ ከ30-50 ዓመት የነበራቸው የመገናኛው ድንኳን አገልጋዮች 8,580 ነበሩ (ቁ. 48)።

## ለ. <u>የተሰጡ ትእዛዛት</u>፡ - (ከምዕ. 5-ምዕ. 10÷10)

<u>ምዕ. 5፡ - ስለ ርኩሰት፤</u>

ርኩስ የሆነ ነገር ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ ካለበት ከሰፈሩ ውጭ መውጣት እንዳለበት ይናገራል። ለምሳሌችንም ይጨምራል።

ቁ. 3 «እኔ በመካከሉ የማድርበትን ሰፈራቸውን እንዳያረክሱ ከሰፈሩ አውጧቸው።»

በተጨማሪ፡ -

- አንድ ሰው ያለአግባብ የሌላውን ንብረት ከወሰደ በወሰደው ላይ 1/5ተኛ ጨምሮ እንዲመልስ ያዛል።
- በትዳር መካከል ታማኝነት እንዳይጓደል ያሳስባል።

<u>ምዕ. 6፡ - ስለ ናዝራዊነት ስእለት ይናገራል።</u>

ምዕ. 5 <u>ከኃጢአትና ከርኩሰት</u> ስለመለየት ሲናገር፣

ምዕ. 6 <u>ለእግዚአብሔር ስለመለየት</u> ይናገራል።

አስቀድመን ከኃጢአትና ከርኩሰት ሳንለይ ለእግዚአብሔር መለየት (መቀደስ) አንችልም።

የናዝራዊነት ስእለት፣ አንድ ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር ለመለየት የሚሳለው ስእለት ነው።

<u>የናዝራዊነት ስእለት፤</u>

1. በፈቃደኝነት የሚደረግ ነው (ቁ. 2)
2. ወይን ጠጅ፣ የሚያሰክር ነገርና ማንኛውም ከወይን የሆነ ነገር ሁሉ አይበላም (ቁ. 3-4)።
3. በራሱ ላይ ምላጭ አይደርስም (ቁ. 5)
4. ወደ ሬሳ አይቀርብም (ቁ.6-7) በአባቱ፣ በእናቱ፣ በወንድሙና በእህቱ ሞት እንኳን ሰውነቱን አያረክስም።

ይህ የናዝራዊነት ስእለት፤ በዘሌ. 21፥10-11 ለሊቀካህኑ እንደተሰጠው ዓይነት ትእዛዝ ነው። ተራው ካህን በእናቱ በአባቱ፤ በወንድ ወይም በሴት ልጁ፣ በወንድሙና በድንግል እህቱ ሞት ጊዜ መርከስ (ሬሳቸውን መቅረብ) ይችላል። ሊቀካህኑ ግን በአባቱና በእናቱ እንኳን መርከስ አይችልም። በዚህ ክፍል (ዘኍ. 6) የምናየው አንድ ተራ እስራኤላዊ የናዝራዊነት ስእለት በሚሳልበት ጊዜ ከሊቀካህኑ የሚጠበቀውን ያህል በማንም ሰው ሬሳ መርከስ (ወደ ሬሳ መቅረብ) እንደማይችል ነው።

5. የናዝራዊነት ስእለቱ ለተወሰነ <u>ወራት</u> ነው።

ቁ. 5 «ራሱን ለመለየት ስእለት ባደረገበት <u>ወራት</u> ሁሉ...»
ቁ. 13 «የመለየቱ <u>ወራት</u> በተፈጸመ ጊዜ...»

<u>የመለየቱ ወራት ሲፈጸም ማድረግ ያለባቸው ነገሮች</u> (ምዕ. 6፣13-20)

1. የሚቃጠል መሥዋዕት
2. የኃጢአት መሥዋዕት
3. የደኅንነት መሥዋዕት
4. የእህል ቁርባንና የመጠጥ ቁርባን ያቀርባል
5. የራሱን ጠጉር በመገናኛው ድንኳን አጠገብ ይላጫል

6. ከጠጉሩም ወስዶ በመሥዋዕቱ እሳት ያቃጥለዋል
7. የመወዝወዝ ቁርባን ያቀርባል።
8. «ከዚያም በኋላ ናዝራዊው ወይን ይጠጣ ዘንድ ይችላል» (ቁ. 20)።

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር ካህናቱ ሕዝቡን የሚባርኩበትን የበረከት ቃል ይሰጣቸዋል።

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡ - ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው፡ - የእስራኤልን ልጆች ስትባርኩአቸው እንዲህ በሉአቸው።

- እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፤
- እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፤
- እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሳ ሰላምንም ይስጥህ።

እንዲሁ ስሜን በእስራኤል ልጆች ላይ ያደርጋሉ፤ እኔም እባርካቸዋለሁ።

✡ ካህናቱ በእግዚአብሔር ስም ሕዝቡን ሲባርኩ የእግዚአብሔር ስም ተጠርቶባቸዋልና እግዚአብሔርን ያንን ባርኮት አክብሮ ሕዝቡን ይባርካል።

## ምዕ. 7፡ - እስራ ሁለት የነገድ አለቆች ያቀረቡት መባና ቁርባን

ሌዋውያን ለአገልግሎታቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች የቀሩት 12 ነገዶች(ኤፍሬምና ምናሴ- እንደ ሁለት ነገዶች ስለተቆጠሩ) እንደሰጡ እናነባለን።

✡ እግዚአብሔር አንድ አገልግሎትን ሲሰጥ ለዚያ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የሚሰጡትን ደግሞ ያዘጋጃል። «ሙሴም ሰረገሎችንና በሬዎችን ተቀብሎ ለሌዋውያን ሰጣቸው። ለጌድሶን ልጆች እንደ አገልግሎታቸው ሁለት ሰረገሎችንና አራት በሬዎችን ሰጣቸው። … ለሜራሪ ልጆች እንደ አገልግሎታቸው

አራት ሰረገሎችንና ስምንት በሬዎችን ሰጣቸው፡፡ ለቀዓት ልጆች ግን መቅደሱን ማገልገል የእነርሱ ነውና በትከሻቸውም ይሸከሙት ነበርና ምንም አልሰጣቸውም» (ቁ. 6-9)፡፡

የሜራሪ ልጆች ሸክማቸው ብዙ ስለነበረ 4 ሰረገሎች አስፈለጋቸው፡፡ 4 ሰረገሎች የተሰጣቸው ከማነነታቸው አንጻር ሳይሆን ከተሰጣቸው ኀላፊነት አንጻር ነበር፡፡ እኛም ልዩ ጸጋ ቢሰጠን ከተሰጠን ኀላፊነት አንጻር እንጂ ከማንነታችን የተነሳ እንዳይመስለን፡፡

- 12ቱ ነገዶች በሙሉ የሰጡት ስጦታ አንድ ዓይነት ነበረ፡፡ የሁሉም ስጦታ አንድ ዓይነት ቢሆንም የእያንዳንዱ ወገን ስጦታ ለየብቻው ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተሰጡት አንድ ዓይነት ስጦታዎች 12ት ጊዜ በየነገዱ ስም ተደጋግመው ተጽፈዋል፡፡

✡ እግዚአብሔር ለእርሱ የምንሰጠውን ስጦታ በጅምላ ሳይሆን በተናጠልና በአክብሮት እንደሚቀበለው ያሳያል፡፡

## ምዕ. 8፡ - የሌዋውያን መቀደስ

«ሌዋውያንን ወስደህ አንፃቸው ታነጻቸው ዘንድ እንዲህ ታደርግላቸዋለህ ኃጢአትን የሚያነጻውን ውሃ እርጫቸው በገላቸውም ሁሉ ምላጭ ያሳልፉ፣ ልብሳቸውንም ይጠቡ፣ ይታጠቡም» (ቁ. 7)፡፡

የሌዋውያን መንጻት በሁለት በኩል ነበረ፡ -

1. ሙሴ ኃጢአትን የሚያነጻውን ውኃ በመርጨት ያነጻቸዋል፡፡
2. እነርሱ ራሳቸው በሰውነታቸው ላይ ያለውን ጸጉር ሁሉ በመላጨትና፣ ልብሳቸውንና ገላቸውን በመታጠብ ራሳቸውን ያነጻሉ፡፡

የእኛንም ሕይወት በምናይበት ጊዜ እግዚአብሔር እኛን የሚያነጻበት ሁኔታ አለ፣ እኛ ደግሞ ራሳችንን የምናነጻበት ሁኔታ አለ፡፡

እግዚአብሔር እንደሚያነጻን፡ -

1ዮሐ. 1፡7÷9 «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡ ... በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡»

እኛ ራሳችንን ማንጻት እንዳለብን፡ -

2ቆሮ 7÷1 «እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፣ የዚህ ተስፋ ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፡፡

ያዕ. 4÷8 «... እናንተ ኃጢአተኞች እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ፡፡»
2ጢሞ. 2÷21 «እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ በያነጻ፣ ለክብር የሚሆን የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል፡፡»

ምዕ. 8÷10 «የእስራኤልም ልጆች በሌዋውያን ላይ እጃቸውን ይጫኑባቸው፡፡»

ሌዋውያን እስራኤላውያንን በሙሉ የሚያገለግሉ ነበሩ፡፡ ነገር ግን በሚቀደሱበት ጊዜ የሚያገለግሉአቸው ሕዝብ በእነርሱ ላይ እጃን መጫን (መባረክ) ነበረበት፡፡

አገልግሎታችን የሠመረ እንዲሆንልን የምናገለግላቸው ሰዎች እኛን ማረክ አለባቸው አገልግሎት በፈቃደኝነትና በወዴታ እንጂ በምናገለግላቸው ሰዎች ላይ በመሰልጠን መሆን የለበትም፡፡

በተጨማሪ ለኃጢአትና ለሚቃጠል መሥዋዕት ሁለት በሬዎችን ካህኑ አሮን ለሌዋውያን ያቀርብላቸዋል (ቁ. 12)፡፡

በዚህ ሁሉ ካለፉ በኋላ ሌዋውያን ለእግዚአብሔር የተለዩ ይሆናል፡፡ ከዚያም በኋላ ማገልገል ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ ምዕራፍ የምንማረው፤ ከአገልግሎት በፊት መቀደስ (ለእግዚአብሔር መለየት) እንደሚገባ ነው፡፡

«ከዚያም በኋላ (ከተለዩ በኋላ) ሌዋውያን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በአሮንና በልጆቹ ፊት አገልግሎታቸውን ይሠሩ ዘንድ ገቡ» (ቁ. 22)፡፡

የሌዋውያንን ለእግዚአብሔር መለየት በምናይበት ጊዜ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሰዎችን( በግልም ሆነ በኅብረት) ለራሱ መለየት እንደሚፈልግ እንረዳለን፡፡

ሀ. በመጀመሪያ እግዚአብሔር <u>አብርሃምን</u> ከዘመዶቹ ለራሱ ሲለየው እናያለን (ዘፍ. 12)

ለ. የአብርሃም የይስሐቅና፣ የያዕቆብ ዘሮች ሕዝብ በሚሆኑበት ጊዜ <u>እስራኤላውያንን</u> ከምድር አሕዛብ ሁሉ መካከል ለራሱ ሲለያቸው እናያለን።

ሐ. ከእስራኤላውያንም መካከል የሌዊን ነገድ (ሌዋውያንን) ለራሱ ሲለይ እናያለን።

መ. ከሌዊም ነገድ የአሮን ቤተሰብ ካህናት ሆነው ለእግዚአብሔር በመለየት እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበረ።

ሠ. ከካህናቱም መካከል አሮን ሊቀካህን በመሆን ከካህናቱ ይልቅ የበለጠ ለእግዚአብሔር የተለየ እንደነበረ እናያለን።

ረ. ከአሮን ቤተሰብም በላይ ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ለማነጋገር ለእግዚአብሔር የተለየ (በቤቱ ሁሉ የታመነ ዕብ. 3÷5) ልዩ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበረ እናያለን።

አሁንም እግዚአብሔር ራሳቸውን ለእርሱ የሚለዩትን ይፈልጋል። «<u>ዛሬ በፈቃዱ</u> ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ (የሚለይ) ማነው?» (1ዜና 29÷5)

## <u>ምዕ.9 ስለ ፋሲካ በዓልና፣ ስለ ደመና እና የእሳት ዓምድ</u>።

- የፋሲካን በዓል በጀመሪያው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን ምሽት ላይ አድርጉ ካላቸው በኋላ፣ በሬሳ የረከሱ ሰዎች ስለነበሩ የፋሲካን በዓል ለማድረግ ለምን እንከለከላለን ሲሉ ሙሴን ይጠይቁታል።

«ሙሴም፡ - እግዚአብሔር ስለ እናንተ የሚያዝዘውን እስክሰማ ድረስ ቆዩ አላቸው» (ቁ. 8)። ከዚህ ቃል የምንማረው እግዚአብሔር ለሙሴ ብዙ ሕግጋትንና ሥርዓቶችን ቢነግረውም አንዳንድ ያልነገረው ነገሮችና ሁኔታዎች ስለነበሩ አዲስ ነገር በሚመጣበት ጊዜ እንደመሰለው መፍረድ ሳይሆን እግዚአብሔርን ጠይቆ አዲስ መመሪያ መቀበል ነበረበት።

እነዚህ በሬሳ ረክሰው የነበሩ ሰዎች የፋሲካን በዓል ከአንድ ወር በኋላ ማለትም በሁለተኛው ወር በአሥራ አራተኛው ቀን ሲመሽ እንዲያከብሩ ሲፈቀድላቸው እናነባለን። ያለ ምክንያት ግን የፋሲካን

በዓል በጊዜው ያላከበረ ቢኖር «ያ ሰው ከሕዝቡ ዘንድ ተለይቶ ይጠፋል <u>የእግዚአብሔርን ቁርባን በጊዜው አላቀረበምና</u> ያ ሰው ኃጢአቱን ይሸከማል» (ዘኍ. 9÷13)።

ከቁ. 15-23 ቀን በደመና ዓምድ ሌሊት በእሳት አምድ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ይመራ እንደነበረ እናነባለን። ይህ ደመናና እሳት ሁልጊዜ በመገናኛው ድንኳን ላይ እንደነበረ ይናገራል። «... በቀን ደመና በሌሊትም የእሳት አምሳል ይሸፍነው ነበር» (ቁ. 16)።

«ደመናውም ከድንኳኑ ላይ በተነሣ ጊዜ በዚያን ጊዜ የእስራኤል ልጆች ይጓዙ ነበር፤ ደመናውም በቆመበት ስፍራ በዚያ የእስራኤል ልጆች ይሰፍሩ ነበር» (ቁ. 17)።
«ደመናው <u>አንድ ቀንም ሆነ ወር ወይም አንድ ዓመት</u> በማደሪያው ላይ ቢቆይ የእስራኤል ልጆችም ያንን ያህል ጊዜ በሰፈራቸው ይቀመጡ ነበር» (ቁ. 22)።
«<u>በቀንም ሆነ በሌሊት</u> ደመናው በተነሣ ጊዜ ይጓዙ ነበር» (ቁ. 21)።

## <u>ከዚህ ክፍል የምንማረው፤</u>

1. እስራኤላውያን <u>የራሳቸው የሆነ</u> ዕቅድና ፕላን የላቸውም ነበር። ነገ ከዚህ ተነስቼ እዚህ ቦታ እሄዳለሁ የሚሉት ነገር የላቸውም።

2. የእነርሱ ኃላፊነት በማናኛው ድንኳን ላይ ያለውን የደመናና የእሳት አምሳል መመልከት እና በዚያ መመራት ብቻ ነበር።

3. <u>በቀንም በሌሊትም</u> ደመናው ከተነሣ ንብረታቸውን ይዘው ደመናውን መከተል ነበረባቸው። <u>ዘወትር ተዘጋጅተው</u> መኖር አለባቸው። በአንድ ሥፍራ ተደላድለውና ከትመው መኖር አይችሉም።

- የእግዚአብሔር ቃል እኛንም፤

«ወገባችሁ የታጠቀ፣ መብራታችሁም የበራ ይሁን እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጁን ሲያንኳኳ <u>ወዲያው</u> እንዲከፍቱለት ... የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ» ይለናል( ሉቃ. 12÷35-36)።

## ምዕ. 10፡ - የመለከት ድምፅ፡

የእስራኤል ሕዝብ በመለከት ድምጽ እንደሚሰበሰብና እንደሚጓዝ እናያለን፡፡ በምዕ.9 ላይ ያየናቸው የደመናና የእሳት አምድ በዓይኖቻቸው ተመልክተው እንዲመሩ ነበረ፡፡ የመለከቶቹ ድምፅ ደግሞ በጆሮአቸው ሰምተው እንዲኖሩ ነበረ፡፡

- መለከቶቹን የሚነፉት የአሮን ልጆች (ካህናቱ) ነበሩ(ቁ.8)፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን ሁለት የብር መለከቶች እንዲሠራ ያዘዋል፡፡

## የእነዚህ መለከቶች ተግባር (ዓላማ) አራት ነበረ

1. ሕዝቡን ለመሰብሰብ (ወደ መገናኛው ድንኳን)
   «ሁለቱም መለከቶች በተነፉበት ጊዜ ማኅበሩ ሁሉ ወደ አንተ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ይሰብሰቡ (ቁ. 3)፡፡
   «አንድ መለከት ሲነፉ ታላላቆቹ የእስራኤል አእላፍ አለቆች ወደ አንተ ይሰበሰባሉ» (ቁ. 4)፡፡
   «ጉባኤውን ለመሰብሰብ ንፉ ነገር ግን ድምፁን ከፍ አታድርጉት» (ቁ. 7)፡፡

2. ሕዝቡ እንዲጓዝ ለማድረግ
   «መለከትንም ከፍ ባለ ድምፅ ስትነፉ በምሥራቅ በኩል የሰፈሩት ይጓዙ» (ቁ. 5)፡፡
   «ሁለተኛውንም ከፍ ባለ ድምፅ ስትነፉ በደቡብ በኩል የሰፈሩት ይጓዙ፤ ለማስጓዝ መለከትን ይነፋሉ» (ቁ. 6)፡፡

3. በጠላት ላይ ሰልፍ ለመውጣት

   - ሁለቱም መለከቶች በአንድ ጊዜ ከፍ ባለ ድምፅ ይነፋሉ፡፡ «በሚገፉችሁም ጠላት ላይ በምድራችሁ ወደ ሰልፉ ስትወጡ ከፍ ባለ ድምፅ መለከቶቹን ንፉ፤ በእግዚአብሔርም በአምላካችሁ ፊት ትታሰባላችሁ፣ ከጠላቶቻችሁም ትድናላችሁ» (ቁ. 9)፡፡

4. በመለከት ድምፅ በዓል ጊዜ (ከአምስቱ በዓላት አንዱ በሆነው በዓል ጊዜ) (ዘሌ. 23፥24)፡፡

   «ደግሞ በደስታችሁ ቀን በበዓላታችሁም ዘመን በወርም መባቻ (ሰባተኛው ወር መባቻ) ... መለከቶቹን ንፉ፤ እነርሱም በአምላካችሁ ፊት ለመታሰቢያ ይሆኑላችኋል» (ቁ. 10)፡፡

ከእነዚህ አራት የመለከት ድምጽ አጠቃቀም የምናስተውለው፡፡

- ሁለቱም መለከቶች በአንድ ጊዜ ሲነፉ ትርጉም አለው፡፡በተናጥል አንዱ ብቻ ሲነፋ ደግሞ ሌላ ትርጉም አለው፡፡
- የመለከቱ ድምጽ ከፍና ዝቅ ሲል ደግሞ ልዩ ትርጉም አለው፡፡

1ቆሮ. 14፡8 «<u>መለከት የማይገለጥን ድምጽ ቢሰጥ ለጦርነትን ይዘጋጃል</u>?»

ይህ የመለከት ድምፅ፣ ግልጽ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔርን ቃል ድምፅ ያሳስበናል፡፡ «እንዲሁ እናንተ ደግሞ የተገለጠውን ቃል በአንደበት ባትናገሩ ሰዎች የምትናገሩትን እንዴት አድርገው ያስተውሉታል» (1ቆሮ 14÷8)፡፡

## ሐ. <u>ጉዞ ከሲና ምድረ በዳ እስከ ቃዴስ በርኔ</u>፡ -
(ምዕ. 10፣11 - ምዕ. 14)

«በሁለተኛውም ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያኛው ቀን እንዲህ ሆነ ደመናው ከምስክሩ ማደሪያ ላይ ተነሣ»( ምዕ. 10÷11)፡፡

ደመናው በተነሣ ጊዜ፡ - በመጀመሪያ በምሥራቅ በኩል የሠፈሩት፡ - የይሁዳ ይሳኮራና የዛብሎን ልጆች ይቀድሙ ነበረ፡ -

- እነርሱንም ተከትለው ሁለቱ የሌዊ ልጆች (ጌድሶናዊያንና የሜራሪ ልጆች) ማደሪያውን ተሸክመው ይሄዱ ነበር፡፡
- ቀጥሎም የሮቤል፣ የስምዖንና የጋድ ነገዶች ይከተሉ ነበረ፡፡ (በደቡብ በኩል ሰፍረው የነበሩ)
- ቀጥሎም የመቅደሱን ዕቃዎች (ታቦቱንም ጭምር) ተሸክመው የነበሩት ቀዓታውያን ይከተሉ ነበር፡፡
- ከእነርሱም በኋላ፤ የኤፍሬም ልጆች፣ የምናሴ ልጆችና፣ የብንያም ልጆች ይጓዙ ነበር፡፡
- በመጨረሻም የዳን ልጆች የአሴር ልጆችና የንፍታሌም ልጆች ይጋዙ ነበር፡፡

ይኼ ሁሉ ወደ 3 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በሥርዓትና በቅደም ተከተል በእግዚአብሔር መሪነት ይጓዝ ነበረ፡፡ «ሙሴም ታቦቱ በተጓዘ ጊዜ «<u>አቤቱ ተነሣ ጠላቶችህም ይበተኑ</u> የሚጠ

ሉህም ከፊትህ ይሸሹ ይል ነበር። ባረፈም ጊዜ <u>አቤቱ ወደ እስራኤል እልፍ አእላፋት ተመለስ</u> ይል ነበር» (ቁ. 35-36)።

በመነሳታችንም ሆነ በማረፋችን፤ በመውጣታችንም ሆነ በመግባታችን እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ እንዲሆን <u>ስሙን መጥራት</u> እንዳለብን ያሳስበናል።

<u>ምዕ.11፡- እስራኤላውያን ሁለት ጊዜ ሲያጉረመርሙ እናያቸዋለን።</u>

«ሕዝቡም ክፉ ሆነው በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ እግዚአብሔርም ሰምቶ ተቈጣ፣ የእግዚአብሔር እሳት በመካከላቸው ነደደች የሰፈሩንም ጳር በላች። ሕዝቡም ወደ ሙሴ ጮኹ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እሳቲቱም ጠፋች» (ቁ. 1-2)።

ይህ ሕዝብ ወደ ሙሴ መጮኽ እንጂ ወደ እግዚአብሔር በቀጥታ መጮኽ አልተማረም። እግዚአብሔርን በግል የሚያውቅ ሕዝብ አልነበረም።

- እንደገና ከቁ. 4 - 35 «የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል? ብለው በእግዚአብሔር ፊት ሲያጉረመርሙና (ቁ.10) በየድንኳኑ ናቸው ደጃፍ ሆነው <u>ሲያለቅሱ</u> እናያለን።

- እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ የማጉረምረምም ለቅሶ እንዳለ እናያለን።

ቁ. 10 «የእግዚአብሔር ቁጣ እጅግ ነደደ፣ ሙሴም ተቆጣ።» በእስራኤላውያን ማጉረምረም የተነሣ፣ ሙሴ ተማርሮ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ እናያለን «... በውኑ ይህን ሁሉ ሕዝብ እኔ ጸነስኩትን? ወለድሁትንስ? በፊቴ ያለቅሳሉና፡ - የምንበላውን ሥጋ ስጠን ይላሉና ለዚህ ሕዝብ ሁሉ የምሰጠው ሥጋ ከወዴት እወስዳለሁ? እጅግ ከብዶኛልና ይህን ሁሉ ሕዝብ ልሸከም አልችልም» (ቁ. 12-14) ።

የሙሴ ምሬት ከባድ ስለነበረ፤ «እንዲህስ ከምታደርግብኝ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ <u>እባክህ ፈጽሞ ግደለኝ</u>» (ቁ.15) ሲል ጸለየ።

- እስከ ሞት ድረስ የማይፈተን የእግዚአብሔር ሰው የሌለ ይመስላል። ኤልያስ «ግደለኝ» ብሎ ሲጸልይ እናያለን።

ጳውሎስ «የሞትን ፍርድ በውስጣችን ሰምተን ነበር» ይላል (2ቆሮ. 1፡9)
ኢየሱስም፡ - «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች» አለ (ማር.14 34)።

የእግዚአብሔር ቃል ሁላችንንም «እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን» ይለናል (ራእይ 2፥10)

ድል ስለነሱ አማኞችም፣ «... ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም» ይላል (ራዕ. 12፥11)።

ሙሴ ያንን የምሬት ጸሎት (የተማረረው ግን በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን በሕዝቡ ላይ ነበረ) ከጸለየ በኋላ እግዚአብሔር ሸክሙን የሚካፈሉ ሰዎችን ሲያዘጋጅለት እናያለን።

«እግዚአብሔር ሙሴን አለው፡ - ከእስራኤል ሽማግሌዎች በሕዝቡ ላይ ሽማግሌዎችና አለቆች ይሆኑ ዘንድ የምታውቃቸውን ሰባ ሰዎች ሰብስብልኝ ወደ መገናኛውም ድንኳን አምጣቸው በአንተ ካለው መንፈስም ወስጄ በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፥ አንተም ብቻ እንዳትሸከም የሕዝቡን ሸክም ከአንተ ጋር ይሸከማሉ»(ቁ.16-17)።

እግዚአብሔር የሙሴን ሸክም የሚካፈሉ ሰባ ሰዎች ሰብስብልኝ ካለው በኋላ፣ «በአንተ ካለው መንፈስም ወስጄ በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ» ማለቱ፣ በሙሴ ላይ ለነበረው ሸክም በቂ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በላዩ እንደነበረ ያሳየናል። ይህ ቢሆንም እንኳን «መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው» ብሎ ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንደተናገረው፣ ሙሴ፣ በቂ መንፈስ በላዩ ቢኖርም እንኳን እንደ ማንኛውም ሰው ሥጋ ለባሽ ስለነበረ ሸክሙ እንደበዛበት እናያለን። ሸክሙን ለሚካፈሉት ሽማግሌዎች እግዚአብሔር የሰጠው መንፈስ ከሙሴ ላይ ወስዶ ነበረ።

የእግዚአብሔር ቃል «ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፣ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው። ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል» 1ቆሮ. 10፣13፣ እንደሚለው ሁሉ ለሙሴም መውጫውን አዘጋጀለት።

የሙሴ ሸክም የሚቃለልበትን መንገድ ካዘጋጀ በኋላ እግዝአብሔር ሙሴን፣ ይህ ሕዝብ የጐመጀውን ያህል ሥጋ «በአፍንጫችሁ እስኪወጣ እስኪሰለቻችሁም ድረስ ወር ሙሉ

ትበላላችሁ» በላቸው ብሎ ይነግረዋል። ሙሴ ይህን ሲሰማ ማመን እንዳቃተው እናያለን። ማመን ያቃተውን ቃል እንዴት ማስተላለፍ ይችላል? «ሙሴም፡ - እኔ በመካከላቸው ያለሁ ሕዝብ ስድስት መቶ ሺህ እግረኛ (የሰልፈኞች ቁጥር ብቻ) ናቸው፤ አንተም ወር ሙሉ የሚበሉትን ሥጋ እኔ እሰጣቸዋለሁ አልህ። እነርሱን የሚያጠግብ የበሬና የበግ መንጋ ይታረድን? ወይስ የባህር ዓሣ ሁሉ ያጠግባቸው ዘንድ ይሰበሰብላቸዋልን? አለ» (ቁ. 21-22)።

ይህ ቃል ከሙሴ አንደበት መውጣቱ ያስገርማል፤ ምክንያቱም እንደ እርሱ የእግዚአብሔርን ድንቅና ተዓምራት የተለማመደና የእግዚአብሔርን ኃይል ያየ የለም። ቀይ ባህር ሲከፈል አይቶአል፣ እግዚአብሔር በ10 መቅሰፍቶች የግብጽን ምድር ሲመታ አይቶአል፣ በእጁ የነበረች በትር እባብ ሆኖ የፈርዖንን በትሮች ሁሉ ስትውጥ አይቷል። ነገር ግን እግዚአብሔር በዚህ ክፍል የተናገረውን ቃል ማመን መታዘዝ ከበደው።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ኤልያስ « እንደ እኛው ሰው ነበር» የሚለን ለዚህ ነው። ሙሴም እንደ እኛው ሰው ነበረ። አንዳንድ ጊዜ አለማመን ቢያስቸግረን እኛም እንደማንም ሰው መሆናችንን ነው የሚያረጋግጠው። መጠንቀቅ ያለብን ነገር ቢኖር ግን፤ ያ አለማመን በልባችን ውስጥ ሥር እንዳይሰድ ነው።

«ወንድሞች ሆይ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንይኖር ተጠንቀቁ» (ዕብ. 3÷12)።

ሙሴ ያንን ያለማመን ቃል ከተናገረ በኋላ፣ እግዚአብሔር አጭር መልስ ይሰጠዋል። «እግዚአብሔር ሙሴን፡ - በውኑ የእግዚአብሔር እጅ አጭር ሆነ? አሁን ቃሌ ይፈጸም ወይስ አይፈጸም እንደሆነ አንተ ታያለህ አለው» (ቁ. 23)።

የሙሴ አለማመን ወይም ጥያቄ የአእምሮ አለመረዳት እንጂ የልብ አለማመን ስላልነበረ ወዲያውኑ እግዚአብሔርን ታምኖ ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል።

«ሙሴም ወጣ የእግዚአብሔርንም ቃሎች ለሕዝቡ ነገረ።» እግዚአብሔር የሚናገረንን ቃል ለሕዝብ መናገር አንዳንድ ጊዜ ትልቅ እምነት ይጠይቃል።

የሙሴ ጥያቄ፤ «እንዴት ሊሆን ይችላል?» የሚል ውስን አዕምሮ መረዳት ሲያቅተው የሚጠይቀው ጥያቄ እንጂ፤ እግዚአብሔር ይህንን ሊያደርግ አይችልም የሚል በልብ ውስጥ ሥር የሰደደ አለማመን አልነበረም። ቅድስት ማርያም፤ «ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?» ብላ፣ ልጅ እንደምትወልድ ያበሰራትን (መልአኩ ገብርኤልን) እንደጠየቀችው ዐይነት የአእምሮ ጥያቄ ነበረ።

በመጨረሻም በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር የባሕርን ድርጭቶች በነፋስ አምጥቶ በሰፈሩ ዙሪያ እንዲከመሩ ሲያደርግና

ሕዝቡ ሥጋውን ሰብስቦ ለመብላት ሥጋው ገና በጥርሳቸው እንዳለ ሳያኝኩትም የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ነድዶ ሕዝቡን በታላቅ መቅሠፍት ሲመታ እናያለን። «የጎመጁ ሕዝብ በዚያ ተቀብረዋልና የዚያ ስፍራ ስም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ» ቁ.34።

<u>የእግዚአብሔር ቃል እኛንም ያስጠነቅቀናል</u>፡ -

1ቆሮ. 10፣6 «እነዚህም ክፉ ነገር እንደተመኙ (እንደጎመጁ) እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን።»
እኛ እንድንመኝ የታዘዝነው በላይ ያለውን ነው።

ቆላ 3፣1-2 «እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።»

## <u>ምዕ. 12፡ - የማርያምና የአሮን በሙሴ ላይ መነሣት</u>።

ቁ. 1-2 «ሙሴም ኢትዮጵያዊቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያዊቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ። እነርሱም በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሮአልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን? አሉ፤ እግዚአብሔርም ሰማ።»

በሙሴ ላይ የተነሱበት <u>የዘረኝነት ስሜት</u> ስለነበረባቸው እንደነበረ እናያለን። «ኢትዮጵያዊቱን አግብቶአልና»

- ነገር ግን ትዕቢትም እንደነበረ ግልጽ ነው። «በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን?» ከሙሴ አናንስም ለማለት ነው።

«እግዚአብሔር ሰማ» የምንናገረውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰማ እያስተዋልን መናገር መልካም ነው። «ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ» (ማቴ. 12÷37)።

ቁ. 3 «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ።» እግዚአብሔር የሚመሰክርለት ሰው የተባረከ ነው።

ቁ. 4 «እግዚአብሔርም <u>ወዲያው</u> ሙሴንና አሮንን ማርያምንም፤ ሦስታችሁ ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡ ብሎ ተናገረ ሦስቱም ወጡ።»

- እግዚአብሔር ለትሑት ሰው (ለራሱ ጥብቅና ለማይቆም ሰው) <u>ወዲያውኑ</u> ጥብቅና ይቆምለታል።

ከቁ. 5-8 እግዚአብሔር አሮንንና ማርያምን ሲገሥጽ ሙሴን ደግሞ ሲያሞግስ እናያለን፡፡ «በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም? ይላቸዋል፡፡

በወንድሞቻችን ላይ የምንናገረው ቃል እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ እንዳይሆን እንጠንቀቅ፣

ከቁ. 9-16 ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች ያሳየናል፤
የእግዚአብሔር ቁጣ (ቁ. 9)
የእግዚአብሔር ቅጣት (ቁ. 10)
የአሮን ንሥሐ (ቁ. 11)
የሙሴ ምልጃ (ቁ. 13)

በማርያም ምክንያት የሕዝቡ መዘግየት (ቁ. 14-16)
«ማርያምም ከሰፈር ውጭ ሰባት ቀን ተዘግታ ተቀመጠች ማርያምም እስክትመለስ ድረስ ሕዝቡ አልተጓዙም፡፡ ከዚያም በኋላ ከሐጼሮት ተጓዙ በፋራንም ምድረ በዳ ሰፈሩ፡፡»

- አመፃችን እኛን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርንም ሕዝብ እንደሚጎዳ ማስተዋል አለብን፡፡ መታዘዛችን ለእግዚአብሔር ሕዝብም ሆነ ለማያምኑ በረከት እንደሚሆን ሁሉ አለመታዘዛችንና አመፃችን ደግሞ በሌሎች ላይ እርግማንን ሊያመጣ ይችላል፡፡

## <u>ምዕ. 13 እና 14፡ - 12 የነገድ አለቆች ወደ ከነዓን ለስለላ መላክ</u>

- አሥሩ ሰላዮች ይዘው ያመጡት ክፉ ወሬ
- የኢያሱና የካሌብ እምነት
- ሕዝቡ የአሥሩን ክፉ ወሬ አምነው ማመጽ
- እግዚአብሔር ሕዝቡን በሙሉ ለማጥፋት መነሣት
- ሙሴ ስለ ሕዝቡ ያቀረበው ምልጃ
- እግዚአብሔር የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ መቅሠፍቱን በቅጣት (አርባ ዓመት በምድረ በዳ መቅበዝበዝ) መለወጥ
- ሕዝቡ ቅጣቱን ሲሰማ እጅግ አዝኖ በአጉል ድፍረት (እግዚአብሔርን ሳይጠብቁ) በጠላቶቻቸው ላይ መውጣትና በጠላቶቻቸው መሸነፍ፡፡

ከእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ርስትን ስለ መሰለል ብዙ ትምህርቶችን እንማራለን፡፡ «ለእስራኤል ልጆች የምሰጣትን የከነዓንን ምድር ይሰልሉ ዘንድ ሰዎችን ላክ» ምዕ. 13፡2፡፡

እግዚአብሔር ተስፋ የገባልንን ርስት (የተስፋ ቃል) ለመውረስ፤

- የተስፋውን ቃል እንቀበላለን
- እንሰልላለን
- እንዋጋለን (በርስቱ ላይ ያሉትን ጠላቶች) (ዘኍ. 13÷30)፡፡
- እንወርሳለን (ዕብ 6፡ 11-12)
- ጠላት ከርስታችን እንዳያስወጣን ጸንተን እንቆማለን (1ዜና 20÷11)
- በራሳችን ኃጢአት ከርስታችን እንዳንፈናቀል እንጠነቀቃለን (ዘዳ. 28÷63)፡፡
- ርስታቸውን ላልወረሱ ወገኖቻችን እንዋጋለን (ኢያሱ 1÷14-15)፡፡

«የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጻፈ» ተብሎ እንደተጻፈው፤ በአዲስ ኪዳንም ዘመን ቅደም ተከተሉ ተመሳሳይ ነው፡፡

ኤፌ. 1፤17-18 «የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን፤ በቅዱስንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ... ታውቁ ዘንድ ነው፡፡»

ቆላ. 1፡12 «... በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ፡፡»

ሐዋ20፡ 32 «አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንፃችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለፀጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ፡፡»

1ጴጥ. 1፤3-5 «... ለህያው ተስፋና፣ ለማይጠፋ እድፈትም ለሌለበት፣ ለማያልፍም ርስት እንደ ምህረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን... ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል፡፡»

ዕብ. 6፥11-12 «በእምነትና በትዕግሥት <u>የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን</u> እንድትመስሉ» ይህንን ርስት <u>በሙላት የምንወርሰው</u> በሰማይ ነው መውረስ የምንጀምረው ግን አሁን ነው። በሰማይ የምንወርሰው ርስት ዋጋው የሚወሰነው አሁን በሥጋ ሆነን (በምድር እያለን) በምንኖረው ሕይወትና በምንሠራው ሥራ ነው።

«እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ» (ራእይ 22፥12)።

«ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (2ዮሐ. ቁ. 8)።

በዘኍ. 13፡25-33 አሥሩ ሰላዮች ያመጡትን የአለማመን ወሬ የእግዚአብሔር ቃል <u>ክፉ ወሬ</u> ይለዋል።

አሥሩ ጠላታቸውን በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል አደረጉ፤ ካሌብና ኢያሱ ግን እግዚአብሔርን በእነርሱና በጠላታቸው መካከል አደረጉ። «ካሌብም ... ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ እንውረሰው አለ» (ቁ. 30)።

አሥሩ ግን «በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብ ላይ መውጣት አንችልም አሉ።» ካሌብ መጨረሻ ላይ እንደ እምነቱ ምድሪቱን ሲወርስ አሥሩ ደግሞ ከሕዝቡ ጋር በምድረ በዳ ሲያልቁ እናያለን። የእግዚአብሔር ቃል «እንደ እምነትህ ይሁንልህ» የሚለው ለዚህ ነው። እምነታችን እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋ ላይ እስከሆነ ድረስ ርስታችንን እንወርሳለን።

«ማኅበሩም ሁሉ ድምፃቸውን አንሥተው ጮኹ ሕዝቡም በዚያ ሌሊት አለቀሱ» (ምዕ 14፥1)።

ለእግዚአብሔር ሕዝብ የምናመጣው ወሬ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያስለቅስ እንዳይሆን እንጠንቀቅ።

በምዕ. 14፥6-9 ኢያሱና ካሌብ የተናገሩትን የእምነት ቃል እናነባለን። ነገር ግን የአሥሩ ወሬ ልባቸውን አቅልጦት ስለነበረ «ማኅበሩ ሁሉ ግን በድንጋይ ይወግሯቸው ዘንድ ተማከሩ» (ቁ. 10) ይላል።

ኢያሱና ካሌብ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ታምነው ስለተናገሩ በድንጋይ ሊወገሩ ደረሱ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን

ታምነን ስለቆምን ሰዎች ሁሉ በእኛ ሊነሱብን ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር ግን በመካከል ቆመላቸው፡፡ <u>እኛ ለእግዚአብሔር ስንቆም እግዚአብሔር ለእኛ ይቆማል</u>፡፡

«የእግዚአብሔር ክብር ለእስራኤል ልጆች ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ተገለጠ፡፡»

ከቁ. 11-20 እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁሉ ሊያጠፋ ሲነሳ ለሙሴም «አንተንም ከእነርሱ ለሚበዛና ለሚጠነክር ሕዝብ አደርግሃለሁ» ሲለው እናነባለን፡፡

ሙሴም እንደ ልማዱ ልዩ የሆነ ምልጃ በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሕዝቡ ያቀርባል፡፡ «... እባክህ እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል፡፡ እግዚአብሔርም አለ፡ - <u>እንደ ቃልህ</u> ይቅር አልሁ፡፡»

- እግዚአብሔር ምን ያህል <u>የባሪያዎቹን ምልጃ እንደሚሰማ ያሳየናል</u>፡፡ ከቁ. 21-38 እግዚአብሔር በመቅሠፍት ፈንታ የተስፋይቱን ምድር እንደማያዩ ይናገራቸዋል፡፡ ምናልባት በዚህ መጽሐፍ ካሉት ጥቅሳች ሁሉ የሚያሳዝነው ጥቅስ ቁ. 25 ነው፡፡ «... በነጋው <u>ተመልሳችሁ</u> በኤርትራ ባህር መንገድ <u>ወደ ምድረ በዳ ሂዱ</u>፡፡» <u>ወደፊት</u> መሄድ የነበረበት ሕዝብ ወደመጣበት ተመልሶ (ወደ ኋላ) እንዲሄድ ታዘዘ፡፡ <u>ማርና ወተት ወደምታፈስ ምድር</u> መሄድ የነበረበት ወደ ምድረ በዳ ሄደ፡፡

«ምድሪቱ በሰለላችሁበት ቀን ቁጥር፣ አርባ ቀን፣ ስለ አንድ ቀንም አንድ ዓመት፣ ኃጢአታችሁን አርባ ዓመት ትሸከማላችሁ፤ ቁጣዬንም ታውቃላችሁ»( ቁ. 34)፡፡

ከቁ. 39-45 እንደምናየው ሕዝቡ ይህንን የእግዚአብሔርን ቁጣና ቅጣት በሰሙ ጊዜ «እጅግ አዘኑ» በአፋቸውም «በድለናል» አሉ፤ ነገር ግን በአጉል ድፍረትና በቁጭት ተነሣስተው ከእግዚአብሔር ሳይሰሙ በጠላቶቻችን ላይ እንወጣለን አሉ፡፡ ሙሴም፤ «እግዚአብሔር በእናንተ መካከል አይደለምና በጠላቶቻችሁ ፊት እንዳትወድቁ አትውጡ» አላቸው፡፡ እነርሱ ግን በአጉል ድፍረት በጠላቶቻቸው ላይ ወጡ «አማሌቃዊና ከነዓናዊ በእነርሱ ላይ ወረዱ፣ መትተዋቸውም እስከ ሐርማ ድረስ አሳደዱአቸው፡፡»

ሕዝቡ በአጉል ድፍረት በጠላቶቻቸው ላይ በወጡ ጊዜ፣ «የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦትና ሙሴ ከሰፈሩ አልተነሡም» (ቁ. 44)።

- እግዚአብሔር ከድፍረት ኃጢአት ይጠብቀን፣ እነዚህ ሰዎች በጠላት ፊት መድፈር በሚገባቸው ጊዜ ፈሩ መፍራት በሚገባቸው ጊዜ ደግሞ ደፈሩ።

# ክፍል 2፡ - የምድረ በዳው መቅበዝበዝ (ዘኍ ምዕ. 15-20)

<u>ወደ ተስፋይቱ ምድር በገቡ ጊዜ የሚጠብቁት ትእዛዝ -(ምዕ. 15</u>)

በምዕ. 15፤1-2 እግዚአብሔር ለሙሴ «ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ...» በማለት ወደ ተስፋይቱ ምድር በገቡ ጊዜ ሊጠ ብቁት የሚገባቸውን ትእዛዛት ይሰጠዋል። ወደ ተስፋይቱ ምድር በእምነት ለመግባት እንቢ ብለው 40 ዓመት በምድረ በዳ እንደሚቅበዘበዙ ከተናገራቸው በኋላ ወዲያውኑ ደግሞ «ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ» ብሎ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊገቡ ላላቸው ከ20 ዓመት በታች ለሆኑት ልጆቻቸው የሚሆን ትእዛዝ ይሰጣቸዋል። በቁ. 18-20 እንደገና «ወደማመጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ እናንተ የምድሪቱን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ... መጀመሪያ ከምታደርጉት ሊጥ አንድ እንጎቻ በማንሣት ቁርባን ታቀርባላችሁ» በማለት ከምድራቸው ፍሬ ለራሳቸው ከመብላታቸው በፊት «ከመጀመሪያው ሊጥ» ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል።

እግዚአብሔር በማንኛውም ነገር <u>የመጀመሪያውን</u> ለእርሱ እንድንቀድስ ይፈልጋል።

<u>የቆሬ የዳታንና የአቤሮን አመጽ -(ዘኍ. 16</u>)

ቆሬ ዳታንና አቤሮን በሙሴንና በአሮን ላይ ስላመጹ በእግዚአብሔር ሲቀጡ እናያለን። ቆሬ ሌዋዊ ሲሆን ከሌዊ ልጆች የቀዓት ዘር ነው። ቀዓታዊያን ደግሞ ከሌሎቹም የሌዊ ልጆች (ከጌድሶንና ከሜራሪ ልጆች) ይልቅ የከበረ አገልግሎት የተሰጣቸው ነበሩ። እንደውም በዘጸ. 6÷18-21 ስንመለከት ቆሬ የሙሴ የአጉት ልጅ እንደነበረ እናነባለን። የመቅደሱን የውስጥ ዕቃዎች በትከሻቸው የሚሸከሙ እነርሱ ነበሩ። ሙሴም ቆሬን «እናንተ የሌዊ ልጆች ስሙ

የእስራኤል አምላክ ከእስራኤል ማኅበር የለያችሁ የእግዚአብሔርንም ማደሪያ አገልግሎት ትሠሩ ዘንድ እንድታገለግሉአቸውም በማኅበሩ ፊት ትቆሙ ዘንድ ወደ እርሱ ያቀረባችሁ አይበቃችሁምን? ... ክህነትንም ደግሞ ትፈልጋላችሁን? (ቁ. 9-10) በማለት፣ የተነሣው በእግዚአብሔር ላይ እንደሆነ ይነግረዋል፡፡ ሙሴ ምንም በምድር ካሉት ሰዎች ሁሉ ትሑት ሰው ነበረ ተብሎ ቢመሰከርለትም የተቆጣባቸው ጊዜያቶች ነበሩ፡፡ ከተቆጣባቸው ጊዜያቶች አንደኛው በዚህ ምዕራፍ ላይ ነው፡፡

ዘኍ 16፣15 «ሙሴም እጅግ ተቆጣ፤ እግዚአብሔርንም ወደ ቁርባናቸው አትመልከት... አለው፡፡»

እግዚአብሔር ያስቀመጠውን ሥርዓትና የሥራ ድልድል ስንቃወም እግዚአብሔርን መቃወማችን ነው፡፡ በሐዋርያት ዘመን ገማልያል በሸንጎ ለነበሩት ፈሪሳውያን «በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ»( ሐዋ.5፣39) ብሎ እንዳስጠነቀቃቸው፤ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስለሚከናወነው አገልግሎት ወይም ስለ እግዚአብሔር ሰዎች ስንናገር በጣም በጥንቃቄና በእግዚአብሔር ፍርሃት መሆን አለበት፡፡ ከሰዎች ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ስንጣላ እንዳንገኝ፡፡

በሙሴና በአሮን ላይ የተነሱትን ሰዎች በእግዚአብሔር መቅሠፍት ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው፡፡ «እነርሱም ለእነርሱም የነበሩ ሁሉ በሕይወታቸው ወደ ሲኦል ወረዱ ምድሪቱም ተዘጋችባቸው፡፡» (ዘኁ. 16፣33) እነርሱን ተከትለው የነበሩትንም 250 ሰዎች የ የእግዚአብሔር እሳት በላቻቸው፡፡

«በነጋውም የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እናንተ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ገድላችኋል ብለው በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ»( ዘኍ. 16፥41)፡፡

ሕዝቡ ያንን ሁሉ መቅሠፍትና ቁጣ በዓይናቸው አይተው እንደገና እነርሱም በሙሴና በአሮን ላይ ተነሡ፡፡ በዚህም ዓመጽ ምክንያት 14, 000 ሕዝብ ተቀሠፈ፡፡

ሙሴና አሮን ግን በእነርሱ ላይ የተነሣው ሕዝብ በሙሉ እንዳይቀሠፍ በእግዚአብሔር ፊት በግምባራቸው ወድቀው ይማልዱላቸው ጀመር፡፡ «እነሆም መቅሠፍቱ በሕዝቡ መካከል ጀምሮ ነበር፤ ዕጣንም ጨመረ ለሕዝቡም አስተሰረየላቸው <u>በሙታንና በሕያዋንም መካከል ቆመ፤</u> መቅሠፍቱም ተከለከለ»
(ዘኍ. 16፣47-48)፡፡

ዘኍ. 17- እግዚአብሔር ሕዝቡ በሙሴና በአሮን ላይ እንደገና እንዲያጉመርሙ ስላልፈለገ እያንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ በትር እንዲያመጣ ያዘል፡ ፡ በእያንዳንዱ በትር ላይ የነገዱን አለቃ ስም እንዲጽፍ

ለሚኬ ይነግረዋል፡፡ በሌዊ ነገድ በትር ላይ የአሮንን ስም እንዲጽፍ ይነግረዋል።

ሙሴም 12ቱን በትሮች በእግዚአብሔር ፊት በምስክሩ ድንኳን ውስጥ አኖራቸው። «በነጋው ሙሴ ወደ ምስክሩ ድንኳን ውስጥ ገባ፤ እነሆም ለሌዊ ቤት የሆነች የአሮን በትር አቆጠቆጠች፤ ለመለመችም፤ አበባም አወጣች፤ የበሰለ ለውዝም አፈራች» (ቁ. 8)። «እግዚአብሔርም ሙሴን፡ - የአሮንን በትር ወደ ምስክሩ ፊት መልስ ማጉረምረማቸው ከእኔ ዘንድ እንዲጠፋ እነርሱም እንዳይሞቱ ለሚያምፁብኝ ልጆች ምልክት ሆና ትጠበቅ አለው» (ቁ. 10)።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የበቀለችው የአሮን በትር ለምልክትና ለማስጠንቀቂያ በታቦቱ ውስጥ ተቀመጠች። በዕብ. 9፤4 «... በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ» ይላል።

በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ አንዳንድ አለመግባባት በሚመጣበት ጊዜ እያንዳንዳችን በትራችንን አንሥተን እርስ በርሳችን ከምንቆራቆስ እያንዳንዳችን በትሮቻችንን በእግዚአብሔር ፊት (ማለትም በጸሎት) ብናቀርብ እግዚአብሔር ፈቃዱንና ሐሳቡን በማያወላውል ሁኔታ ይገልጽልናል።

## <u>ዘኁ. 18፡ - እግዚአብሔር ለአሮን የሰጠው መመሪያ።</u>

በቁ. 2 «ደግሞም የአባትህን የሌዊን ነገድ ወንድሞችህን ከአንተ ጋር አቅርብ ከአንተም ጋር በአንድነት ይሁኑ <u>ያገልግሉህም</u>» ይለዋል። በዚህ ጥቅስ፤ ሌዋውያን «ያገልግሉህ» እንጂ «ያገልግሉኝ» አላለውም። የእግዚአብሔርን ሰዎች ማገልገል እግዚአብሔርን እንደማገልገል ነው። በመጀመሪያ በታማኝነት የእግዚአብሔርን ሰዎች ሳናገለግል ለእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ መሆን አንችልም። በመጽሐፈ ኢያሱ 1፥1 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ኢያሱን «የሙሴ አገልጋይ» ብሎ ይጠራዋል። ኢያሱ በቀጥታ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከመሆኑ በፊት የሙሴ አገልጋይ ነበረ። እግዚአብሔርም ታማኝነቱን አይቶ የበለጠ አከበረው። የእግዚአብሔር ቃል፤ በሌላው ገንዘብ ካልታመናችሁ የራሳችሁን ማን ይሰጣችኋል የሚለው ለዚህ ነው። እግዚአብሔር የራሳችን የሚሆን ኃላፊነት የሚሰጠን በሌላው ሰው ኃላፊነት ሥር ገብተን በታማኝነት ካገለገልን በኋላ ነው።

በተጨማሪም በዘኁ. 18፡3 «እነርሱም <u>ትእዛዝህን</u> የድንኳኑንም ሁሉ አገልግሎት ይጠብቁ» ይለዋል። በዚህም ጥቅስ «ትእዛዝህን»

እንጂ «ትእዛዜን» አይለውም:: በዓይናችን የምናየውን የእግዚአብሔር ሰው መታዘዝ የማንችል ከሆነ የማናየውን እግዚአብሔርን እንዴት እንታዘዛለን?

ቁ. 7 «አንተም ከአንተም ጋር ልጆችህ ለመሠዊያው ሥራ የሚሆነውን ሁሉ በመጋረጃውም ውስጥ የሚሆነውን ታደርጉ ዘንድ ክህነታችሁን ጠብቁ አገልግሉም...» አንድ ካህን በእግዚአብሔር ፊት ለማገልገል ክህነቱን መጠበቅ አለበት:: እንደ ኤሊ ልጆች ክህነትን አርክሰም ማገልገል ይቻላል፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣት እንጂ ደመወዝ የለውም::

በዘኍ. 18፡20-24 አሮንና ሌዋውያን በእስራኤል ልጆች መካከል ድርሻና ርስት እንደሌላቸው ይነግራቸዋል:: «እግዚአብሔርም አሮንን አለው: - በምድራቸው ርስት በመካከላቸውም ድርሻ አይሆንልምህም በእስራኤል ልጆች መካከል ድርሻህና ርስትህ እኔ ነኝ::» ከምድራዊ ርስት ይልቅ እግዚአብሔር ራሱ «ድርሻህና ርስትህ እኔ ነኝ» ሲል ምን ያህል መታደል ነው:: «ለሌዊም ልጆች እነሆ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ስለሚያገለግሉ የእስራኤልን ልጆች አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ:: ... በእስራኤልም ልጆች መካከል ርስት አይወርሱም::»

እግዚአብሔር ለአሮንና ለሌዋውያን በእስራኤል ልጆች መካከል ርስት ያልሰጠበትን ምክንያት በምናይበት ጊዜ የምንረዳው: - ሰማያዊን አገልግሎት ስለሚያገለግሉ በምድራዊ ነገርና ኑሮ ተጠላልፈው ሃሣባቸው፣ ኃይላቸውና፣ ጊዜያቸው ከእግዚአብሔር አገልግሎት እንዳይከፈል፣ በሙሉ ልባቸው፣ ነፍሳቸውና ኃይላቸው ማገልገል እንዲችሉ ነው:: በአሁኑ ቋንቋ ብንናገር፣ ከማንም ጋር ስለ ርስትና ንብረት ተሟግተው ፍርድ ቤት መሄድ የለባቸውም «ርስታቸው እግዚአብሔር ነውና»

ሌዋውያን ከእስራኤል ልጆች አሥራትን ከተቀበሉ በኋላ የአሥራትን አሥራት ማቅረብ እንዳለባቸው በቁ. 26 ላይ ያዛቸዋል::

<u>ዘኍ. 19: - በሬሳ የረከሱ ሰዎች የሚነጹበት ሥርዓት</u>::

በምዕ. 16 በተደረገው ዓመጽ ምክንያት ብዙ ሰዎች ሞተው ስለነበረ ያንን ሁሉ ብዙ ሺህ ሬሳ ሲያነሱና ሲቀብሩ በሬሳ የረከሱ ብዙ ሰዎች ስለነበሩ የሚነጹበትን መንገድ ያሳያቸዋል::

የሚነጹበትም መንገድ: - አንድ መልካም፣ ነውር የሌለባት፣ ቀንበርም ያልተጫነባት ቀይ ጊደር ወደ ካህኑ ያመጣሉ:: እርስዋም

ከሰፈር ውጭ ትታረድና ካህኑ አልዓዛር ከደምዋ በጣቱ ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ፊት ሰባት ጊዜ ይረጨዋል። ጊደሪቱም፣ ቁርበትዋ፣ ሥጋዋ፣ ደምዋ፣ ፈርስዋም ሁሉ ይቃጠላል አመድዋም ይሰበሰብና በሬሳ በረከሱ ሰዎችና ዕቃዎች ላይ ርኩሰትን ከሚያነፃ ውኃ ጋር ሆኖ ይረጫል። የተረጨባቸውም ሰዎችና ዕቃዎች ንጹህ የሆናሉ።

እያንዳንዱ በሬሳ የረከሰ ሰው ወደ ካህኑ ቀርቦ ትኩስ ደም በማፍሰስ የብዙ እንስሳት ደም ከመፍሰሱ ይልቅ እግዚአብሔር ያዘጋጀው መንገድ የዚያች የቀይ ጊደር አመድ(ውስጡ የጊደርዋ ደምም ተቃጥሎ ስላለበት) ከውኃ ጋር ሆኖ በመረጨት ብቻ ለብዙዎች ምነፃት ምክንያት ሆነ።

የዚህ ሥርዓት ምሳሌነት «ከኃጢአት ሁሉ የሚያነፃው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም» እንደሆነ በዕብ. 9፣13-14 እናነባለን። «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንፃት የሚቀድሱ ከሆነ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዝአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነፃ ይሆን?»

ከዚህ ምዕራፍ ሌላ የምናየው ነገር፡ - ይህንን የሚያነፃ አመድ ያለበትን ውኃ የሚያዘጋጁ ሰዎች በዝግጅቱ ውስጥ ማድረግ ያለባቸውን ተሳትፎ ካደረጉ በኋላ «እስከማታ ድረስ ርኩስ ይሆናሉ»ይላል፡፡

ቁ.7 «ካህኑም ልብሱን ያጥባል ገላውንም ይታጠባል ከዚያም በኋላ ወደ ሰፈሩ ይገባል፣ ካህኑም እስከ ማታ ርኩስ ይሆናል።»

ቁ. 8 «(ጊደሯን) ያቃጠላትም ሰው ልብሱን በውኃ ያጥባል ገላውንም በውኃ ይታጠባል እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ይሆናል።»

ቁ. 10 «የጊደሪቱንም አመድ ያከማቸ ሰው ልብሱን ያጥባል... እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።»

ቁ. 21 «የሚያነፃውን ውኃ የሚረጭ ሰው ልብሱን ያጥባል... እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።»

ከዚህ የምንማረው፣ በአገልግሎት ውስጥ የሚገባንን እያደረግን እንኳን በሃሳብ፣ በአንደበት፣ በድርጊት መርከስ እንደምንችል ነው። «ኃጢአት የለብንም ብንል ውሸተኞች ነን» (1ዮሐ. 1፥8)። ስለዚህ ከአገልግሎታችን በኋላ እንኳን «እኛ የማንጠቅም ባሪያዎች የሚገባንን

አደረግን» ብለን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ራሳችንን ዘወትር ማንፃት አለብን፡፡

ሳንነፃ እንዲሁ ብንቀጥል፣ «ርኩሱም የሚነካው ነገር ሁሉ ርኩስ ይሆናል» (ቁ. 22) ስለሚል ለሌሎች በረከት ከመሆን ይልቅ እርግማን እንሆናለን፡፡ ሕይወታችንን ሳናነፃ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ምንም ነገር (ማንኛውንም አገልግሎት) አንነካ፣ ምክንያቱም የምንነካውን ነገር ሁሉ እናረክሳለን፡፡

ዘኍ. ምዕ. 20፡ - የማርያምና የአሮን መሞት

ይህ ምዕራፍ፣ ሙሴና አሮን ወደ ተስፋይቱ ምድር አትገቡም የተባሉበት ምዕራፍ ነው፡፡
ከቁ. 1 ስለማርያም መሞትና መቀበር ይጠቅሳል፡፡
በቁ. 2-9 ሕዝቡ የሚጠጡት ውኃ ስላልነበራቸው ሙሴን ይጣሉታል፡፡ እስራኤላውያን እንደ ልማዳቸው ያጉረመርማሉ እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን፡ - «ማኅበሩን ሰብስቡ፣ ድንጋዩም ውኃን እንዲሰጥ እነርሱ ሲያዩ ተናገሩት ከድንጋዩም ውኃ ታወጣላቸዋለህ» (ቁ. 8) ይላቸዋል፡፡ ነገር ግን ሙሴና አሮን እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ድንጋዩን ሜናገር ሳይሆን ሜኤ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ ይመቃዋል፡፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሕዝቡን ይዘው እንዳይገቡ ይናገራቸዋል፡፡ «በእስራኤል ልጆች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁምና ስለዚህ ወደ ሰጧችሁ ምድር ይህን ጉባኤ ይዛችሁ አትገቡም አላቸው»( ቁ. 12)፡፡
በመዝ. 106፣32-33 ሕዝቡ ሙሴን እንዳስመረሩት ይናገራል፡፡

«በክርክር ውኃ ዘንድም አስቆጡት
መንፈሱን አስመርረውታልና
ስለእነርሱም ሙሴ ተበሳጨ
በከንፈሮቹም በስንፍና ተናገረ፡፡»

ሙሴ በሕዝቡ ማማረር ብቻ ሳይሆን፣ ባለፉት ዘመናት በሙሉ የተለማመደውና እግዚአብሔር ተዓምራት ሲያደርግ ያየው በበትሯ በኩል ስለነበረ፣ እግዚአብሔር አዲስ ልምምድ ውስጥ እንዲገባ፣ «ድንጋዩም ውኃ እንዲሰጥ እነርሱ እያዩ ተናገሩት» ብሎ ያዘዘውን ትእዛዝ ከመፈጸም ይልቅ የብዙ ዓመታት ልምምድ የሚነግረውን ሰምቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ ሲመታ እናያለን፡፡ እኛም ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር አዲስ ልምምድ ውስጥ ሊያስገባን ሲፈልግ ከእግዚአብሔር አዲስ መመሪያ ይልቅ በራሳችን ልምምድ መደገፍ ይቀለናል፡፡ ያ አዲስ መመሪያ አዲስ እምነት ይጠይቃል፡፡

በልምምዳችን መሄድ ግን ምንም እምነት አይጠይቅም። ስለዚህ ነው «በእስራኤል ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ በእኔ አላመናችሁምና» ያላቸው።

ከቁ.14-21 እስራኤል በኤዶምያስ ምድር ለማለፍ የኤዶምያስን ንጉሥ ፈቃድ ቢጠይቁ እንቢ ይላቸዋል። ኤዶምያስ የኤሳው ዝርያ ነው (ዘፍ. 36፥1፤ ዘዳ. 2፥4-6፤ ዘዳ. 20፥14)።

ከቁ. 22-29 የአሮን መሞት የአልአዛር መተካት፤

የአሮን ሞት የ40ውን ዓመት የምድረበዳ መቅበዝበዝ ይደመድማል።

ዘኁ. 33፣38 «ካህኑም አሮን በእግዝአብሔር ትእዛዝ ወደ ሖር ተራራ ላይ ወጣ፣ በዚያም የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ምድር ከወጠ በኋላ በአርባኛው ዓመት በአምስተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ሞተ።»

## ክፍል 3፡ - አዲሱ ትውልድ- ምዕ. 21-36

ይህ ሦስተኛው ክፍል እንደ አንደኛው ክፍል በሦስት ይከፈላል።

1. አዲሱ ጉዞ (ምዕ. 21-25)
2. አዲሱ የሕዝብ ቆጠራ (ምዕ. 26-27)
3. አዲሱ መመሪያ (ምዕ. 28-36)

በዚህ ክፍል የምናየው ከግብጽ የወጣው ትውልድ በሙሉ አልቆ ልጆቻቸው በእነርሱ ፈንታ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ጉዞ ሲያደርጉና ሲዘጋጁ ነው። አሮንና ማርያም ሞተዋል፤ ሙሴ ደግሞ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የመሪነቱን ኃላፊነት ለኢያሱ ያስተላልፋል።

1. አዲሱ ጉዞ --(ምዕ. 21-25)

- ከቃዴስ እስከ ሞአብ ምድር ድረስ የነበረው ጉዞ የፈጀው ከ4 እስከ 5 ወራት ነበር።

አሮን ከሞተ በኋላ አንድ ወር አልቅሰውለት ጉዞ ይጀምራሉ። አሮን የሞተው በ40ኛው ዓመት በአምስተኛው ወር ሲሆን፤ ወደ ሞዓብ ምድር የደረሱት ደግሞ በ40ኛው ዓመት በ11ኛው ወር ነው (በዘዳ. 1፣3-5)። ኤዶም (የኤሳው ዝርያዎች) በምድራቸው እንዳያልፉ ባይከለክሏቸው ኖሮ በአጭር ገዜ ውስጥ ይደርሱ ነበር።

ምዕራፍ 21፤

ሀ. <u>የእስራኤላውያን የመጀመሪያ ድል</u>፤

እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በኋላ በዘጸአት 17 ላይ ኢያሱ አማሌቅን ድል ከማድረጉ ሌላ፣ እስራኤላውያን በ40 ዓመታት ውስጥ ተዋግተው ድል ሲያደርጉ አናይም።

«እስራኤልም ለእግዚአብሔር፡ - እነዚህን አሳልፈህ ብትሰጠኝ ከተሞቻቸውን እርም ብዬ አጠፋለሁ ብሎ ስእለት ተሳለ። እግዚአብሔር የእስራኤልን ድምጽ ሰማ ከነዓናውያንንም አሳልፎ ሰጣቸው» (ምዕ. 21÷2)። ከ38 ዓመታት በፊት አባቶቻቸው በእግዚአብሔር ላይ አምጸው በአጉል ድፍረት እግዚአብሔር ሳያዛቸው ጦርነት ሄደው በአማሌቃውያንና በከነዓናውያን ተመትተው እስከ ሔርማ ድረስ ተሳድደው ነበር (ምዕ. 14÷42-45)። አሁን ግን እግዚአብሔር ለአዲሱ ትውልድ ያንን መሸነፍ ወደ ድል ይለውጥላቸዋል። «እግዚአብሔርም የእስራኤልን ድምጽ ሰማ፤ ከነዓናውያንንም አሳልፎ ሰጣቸው ... የዚያንም ሥፍራ ስም ሔርማ ብለው ጠሩት።»

ከ38 ዓመታት በፊት አባቶቻቸው የተሸነፉት በከነዓናውያን ነበር፤ የተሸነፉበትም ሥፍራ ሔርማ ነበረች። እግዚአብሔር ባሸነፉአቸው ጠላቶች ላይ በተሸነፉበት ቦታ ድልን ሰጣቸው።

ለእኛም እግዚአብሔር በተሸነፍንበት ቦታ ድልን ሊሰጠን ይወዳል ከየትም ቦታ ተሸንፈን እንድንወጣ ፈቃዱ አይደለም። በክርስቶስ ኢየሱስ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን» (2ቆሮ. 2÷14) ነው የሚለው። ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በራእ. 2፣5 «እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውን ሥራህን አድርግ» ይለዋል። የወደቅንበት ቦታ ተመልሰን ሄደን በንሥሐና በእምነት መሸነፋችንን በድል እንዲለውጥልን መለመን አለብን።

ከዚህ ክፍል የምንማረው፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ውጭ በምንሆንበት ጊዜ እንሸነፋለን፤ ነገር ግን እንደገና በእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ውስጥ ስንገባ ድልን እንጐናጸፋለን።

ለ. <u>የእስራኤላውያን ስለ መና ማጉረምረምና የእግዚአብሔር ቅጣት፤</u>

ከቁ.4-9 የምናየው፤ የኤዶምያስን ምድር መዞር ስለነበረባቸው «የሕዝቡ ሰውነት ከመንገዱ የተነሣ ደከመ። ሕዝቡም በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ፡ - በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብጽ ለምን

አወጣችሁን? እንጀራ የለም ውኃ የለም ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ ብለው ተናገሩ።»

ባጉረመረሙ ጊዜ እግዚአብሔር ተናዳፊ እባቦችን በሕዝቡ ላይ ሲሰድ እናያለን። ከሕዝቡም ብዙ ሰዎች ሞቱ። ሕዝቡ ንስሐ በገቡ ጊዜ ሙሴ ስለ ሕዝቡ ሲጸልይ እግዚአብሔር ሙሴን፡ - «እባብ ሥርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው። ሙሴም የናስ እባብ ሥርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ» (ዘኍ. 22፥8-9)።

ይህ የናስ እባብ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ መሰቀል ምሳሌ እንደሆነ (ዮሐ. 3፥14-15) ያመለክታል።

«ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል» ዮሐ. 3፥14-15።

በ2ኛ ነገ. 18፥4 ላይ ሙሴ የሠራውን የነሐስ እባብ እስከዚያ ዘመን ድረስ አስቀምጠውት እንደ ጣዖት ያጥኑለት እንደ ነበረ እናነባለን። «... እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ።» ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በአንድ ዘመን ለተወሰነ ጊዜና ዓላማ የተጠቀመበትን ነገር እኛ ላልተወሰነ ጊዜና ለማይገባ ዓላማ ስንጠቀምበት፣ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጣዖት ሆኖብን ስንሰናከልበት እንገኛለን። እግዚአብሔር ባለፉት ዓመታት የተጠቀመበትን መንገድ አሁንም በእኛ ዘመን ካላደረገ ብለን ልናጥንለትና እንቅፋት ሊሆንብን አይገባም። በአንድ ዘመን ለፈውስ የነበረው በሌላ ዘመን መሰናከያ ሆነ። ትልቁ መመሪያ፤ ለምናደርገው ነገር ሁሉ፣ እግዚአብሔር ተናግሮኛል ወይ? ወይስ እከሌን ከዘመናት በፊት ተናግሮት ይህንን ስላደረገ እኔም የእርሱን ድርጊት ልከተል? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ነው። ሙሴ ያደረገው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ ነበረ ያደረጉት።

ሐ. <u>የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ፤</u>

በቁ. 14- «የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ» የሚባል መጽሐፍ እንደነበረ ይናገራል። ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ጦርነት የሚዋጉ ሰዎች ታሪክ የሚጻፍበት ሳይሆን አይቀርም። በእግዚአብሔር መንግሥት የተለያዩ መጽሐፍት እንዳሉ በዮሐ. ራእ 20፣12 እናያለን

«ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋን ፊት ቆመው አየሁ፣ መጽሐፍትም ተከፈቱ፣ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፡፡ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ፡፡»

እኛም የእግዚአብሔርን ጦርነት የምንዋጋ ከሆነ በእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ ከሚጻፉት ውስጥ እንሆናለን፡፡

መ. ድል (የውሃ መፍለቅ) በዝማሬ፤

ከቁ. 16-18 እግዚአብሔር ለሙሴ «ሕዝቡን ሰብስብ ውኃን እሰጣቸዋለሁ» ይለዋል፡፡ «በዚያም ጊዜ እስራኤል ይህን መዝሙር ዘመረ፡ - አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ፤ እናንተ ዘምሩለት፤ በበትረ መንግሥት በበትራቸውም የሕዝብ አዛውንቶች ያጐደጐዱት፣ አለቆችም የቆፈሩት ጉድጓድ፡፡»

ከግብጽ ወጥተው የኤርትራን ባህር ካቋረጡ በኋላ ከዘመሩት መዝሙር ሌላ እስራኤላውን ለ40 ዓመታት መዝሙር ዘመሩ ሲባል አንሰማም፡፡ በዚህ ክፍል ግን ችግራቸውን በማጉረምረም ሳይሆን በመዝሙር ማሸነፍ እንደሚችሉ የተማሩ ይመስላል፡፡

በምድረ በዳ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ሦስት ጊዜ ውኃን አፍልቆላቸዋል፡፡

1. ዘጸ. 17÷6 -ዓለቱን ትመታለህ፡ - ውኃም ይወጣል
2. ዘኁ. 20÷8 - ድንጋዩን ተናገሩት፡ - ውኃ ታወጣላቸዋለህ
3. ዘኁ. 2÷16-18- እስራኤል ዘመረ፣ አዛውንቶች አጐደጐዱት፣ አለቆች ቆፈሩት፡ - ምንጭም ፈለቀ፡፡

በእነዚህ በሦስት ጊዜያት፣ የእግዚአብሔር ዓላማ እምነታቸው እያደገ እንዲሄድ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

- በመጀመሪያ ሙሴ ዓለቱን ሲመታው ውኃ ፈለቀ፤
- በሁለተኛው ጊዜ ሙሴና አሮን የተባሉትን አላደረጉም እንጂ፣ በቃል ብቻ ዓለቱን ሲናገሩት ውኃ ይፈልቅ ነበረ፡፡ ከመጀመሪያው ይልቅ ሁለተኛው የበለጠ እምነት ይጠይቃል ማለት ነው፡፡

- በሦስተኛው ጊዜ ግን፣ ሙሴ ሳይሆን እስራኤላውያን ራሳቸው፣ ዘመሩ ምንጭም ፈለቀ ካለፉት ሁለት ጊዜያት የላቀ እምነት ይጠይቃል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሊያስተምራቸው የፈለገው በዝማሬ ውኃ እንደሚፈልቅ ነበረ። እኛም በሕይወታችንና በምናልፍባቸው የተለያዩ ደረቅ ሁኔታዎች ለጌታ ስንዘምርለት የህይወት ውኃ ምንጭ ይፈልቃል። «በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ዘምሩ» (ኤፌ. 5፥19)።

ሠ. ከድል ወደ ድል፣

ከቁ. 21-35፤ የዝማሬን ህይወት ከጀመሩ በኋላ እግዚአብሔር በሁለት ነገሥታት ላይ ድልን ሰጥቶ ምድራቸውን ወረሱ። እነዚህም ድል የተነሱት ነገሥታት የአሞራውያን ንጉሥ ሴዎንና የባሳን ንጉሥ ዐግ ናቸው።

የበለዓም ታሪክ፤ ከዘኍ. ምዕ. 22-24

በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች፤ አንድ በለዓም የሚባል ሁለት መልክ ያለውን ሰው እናያለን። በአንድ በኩል የእግዚአብሔርን ድምጽ ማስማት የሚችል፣ ከሕያው እግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርግ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ላይ መጥቶ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገር (ዘኍ. 24፥2) ነቢይ ነበረ። በ2ጴጥ. 2፣15 ነቢይ ተብሎ ተጠርቷል። በአንፃሩ ግን እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ የአመጻን ደሞዝ የሚወድ፣ በአንደበቱ የእግዚአብሔርን ቃል ቢናገርም ልቡ ለእግዚአብሔር ቃል ያልተገዛና ያልተንበረከከ፣ እግዚአብሔር እርግማኑን ወደ በረከት ባይለውጠው ኖሮ እስራኤልን (የእግዚአብሔርን ሕዝብ) ከመርገም ወደ ኋላ የማይል፣ በመጨረሻም እሥራኤልን እንዲረግም እግዚአብሔር ስላልፈቀደለት ለሞዓባውያን ክፉ ምክርን በመምከር እስራኤላውያንን በጣዖታቸውና በርኩሰታቸው እንዲያስቱአቸው ያደረገ መተተኛ ነቢይ እንደነበረ ከዘኍ. 31፥16 እንረዳለን።

ከእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ሌላ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ስለዚህ ሐሰተኛ ነቢይ ተጽፎአል። (ኢያሱ 13፣22) «ከገደሉአቸው ሰዎች ጋር የእስራኤል ልጆች ምዋርተኛውን የቢዖርን ልጅ በለዓምን በሰይፍ ገደሉት።»

በዘኍ. 23÷10 ላይ በለዓም « ... የጻድቃንን ሞት እኔ ልሙት፣ ፍጻሜዬም እንደ እርሱ (እንደ ያዕቆብ ወይም እስራኤል) ፍጻሜ ትሁን።» ብሎ ነበረ ነገር ግን ጻድቅ ሳይሆኑ የጻድቅን ሞት መሞት አይቻልምና እንደ ተመኘው የጻድቅን ሞት ሳይሆን የኃጥአንን ሞት ሞተ።

የእግዚአብሔር ቃል፡ - በምሳ. 10፣24 ላይ «የኀጥእ ሰው ፍርሃት በላዩ ይመጣበታል፤ ለጻድቃንም ምኞታቸው ትሰጣቸዋለች።» የሚለው ለዚህ ነው።

«እነሆ እነዚህ (የሞአብ ሴቶች) በፌጎር ምክንያት በበለዓም ምክር እግዚአብሔርን ይበድሉ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ዕንቅፋት ሆኑ ስለዚህም በእግዚአብሔር ማኅበር ላይ መቅሠፍት ሆነ» (ዘኍ. 31÷16)። በማለት በለዓም እሥራኤልን መርገም ስላልሆነለት ክፉ ምክርን ለባላቅ መክሮ የሞዓብ ሴቶች የእሥራኤልን ወንዶች እንዲያሳሳቱ እንዳደረገ ይነግረናል።

በዚህም ክፉ ምክር ምክንያት እሥራኤላውያን በወጥመድ ውስጥ ወደቁ (በዘኍ. 25÷1-2)፤ «እስራኤልም በሰጢም ተቀመጡ ሕዝቡም ከሞዓብ ልጆች ጋር ያመነዝሩ ጀመር። ሕዝቡንም ወደ አምላኮቻቸው መሥዋዕት ጠሩ ሕዝቡም ሁሉ ወደ አምላኮቻቸው ሰገዱ።» በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በእሥራኤል ላይ ነደደ፣ 24,000 ሰዎች በመቅሠፍት ሞቱ (ዘኍ. 25)። በዘኍ. 22 እስከ 24 ያሉትን ምዕራፎች ስናነብ የበለዓም ዓመጽ ግልጽ ሆኖ አይታይም፤ ምክንያቱም በለዓም አፋዊ ነቢይ ስለሆነ የሚናገረው ነገር ሁሉ ከመታዘዝና ከቅንነት ይመስላል። በሌላ ሥፍራዎች ስለ እርሱ የተጻፉትን ስናነብ ግን የአፉ መታዘዝ ሳይሆን የልቡ አመጽ ጉልህ ሆኖ ይታያል።

ለምሳሌ በኢያሱ 24÷9-10፤ «የሞአብ ንጉሥ የሴፎር ልጅ ባላቅ ተነሥቶ ከእሥራኤል ጋር ተዋጋ፣ እንዲረግማችሁም የቢዖርን ልጅ በለዓምን ልኮ አስጠራው። እኔ ግን በለዓምን መስማት አልወደድኩም፣ እርሱም ፈጽሞ ባረካችሁ፣ እኔም ከእጁ አዳንኳችሁ።» በማለት በልቡ እሥራኤልን ረግሞ የአመጻን ገጸ በረከት መቀበል ፈልጎ እንደነበረ ያሳየናል። እንዲሁም ዘዳ.23፡5 «ነገር ግን አምላክህም እግዚአብሔር በለዓምን ይሰማ ዘንድ አልወደደም፤ አምላክህም እግዚአብሔር ወድዶሃልና እርግማኑን በረከት አደረገልህ» ይላል።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ በሦስት ቦታዎች ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ተጠቅሶአል፤

1. **የበለዓም መንገድ-** 2ጴጥ. 2፣15

2 **የበለዓም ስህተት - ይሁዳ**.11

3.**የበለዓም ትምህርት -ራእ** 2፡ 14

2 **ጴጥ**.2፡ 15 «**ቅንን መንገድ ትተን ተሳሳቱ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ እርሱ የዓመፃን ደመወዝ ወደደ ነገር ግን ስለመተላለፉ ተዘለፈ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ**።»

**ይሁዳ** 11 «**ወዮላቸው በቃየን መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለብልዓም ሽተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል**።»

**ራእ**። 2፡14 « **ዳሩ ግን ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያ ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበለዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋር ስላሉ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ**።

- **የበለዓም መንገድ**-የአመፃን ደመወዝ መውደድ
- **የበለዓም** ስህተት - **የእግዚአብሔርን** ሐሳብ ለማስቀየር መሞከር
- **የበለዓም** ትምህርት -ሴሰኝነት

**ከእነዚህ** ጥቅሶች እንደምንረዳው በለዓም **ለእግዚአብሔር** ም ለገንዘብም ለመገዛት ሞክሮአል። **የእግዚአብሔር** ቃል «ለሁለት ጌቶች ልትገዙ አትችሉም **ለእግዚአብሔርና** ለገንዘብ ልትገዙ አትችሉም።» እንደሚለው ሁሉ **የበለዓም** ፍፃሜ ለገንዘብ መገዛት ነበር።

ከዚህ ሰው ታሪክ የምንማረው ነገር ቢኖር **እግዚአብሔር** የሚያየው በአፋችን የ**እግዚአብሔር**ንር ቃል መናገራችንና በአፋችን **እግዚአብሔርን** መታዘዛችንን ሳይሆን በልባችን ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ መገዛታችንን ነው **እግዚአብሔር** አፋዊ ከሆነ ሕይወትና አገልግሎት ይጠብቀን።

የዚህን ሰው ታሪክ ከ**እግዚአብሔር** አንጻር ስናየው ግን **እግዚአብሔር** ስለ ሕዝቡ ሲል ሐሰተኛና መተተኛ በሆነ ሰው በኩል እንኳ ድንቅ የሆኑ የበረከትና የትንቢት ቃሎችን አስተላልፎአል። ስለ **እግዚአብሔር** ባህርይ እውነትና ድንቅ የሆነ ቃልን ተናግሮአል።

**ዘኍ**.23፡19 «ሐሰትን ይናገር ዘንድ **እግዚአብሔር** ሰው አይደለም ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም፡፡»

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም፤

**ዘኍ**.24፡17 «አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ከእስራኤል በትር ይወጣል፡፡»

**ዘኍ**.24፡19 «ከያዕቆብም የሚወጣ ገዥ ይሆናል´ በማለት ትንቢታዊ ቃልን ተናግሮአል፡፡

## ዘኍ.25፡ የእሥራኤል በመቅሠፍት መመታትና የፊንሐስ ቅናት

ከቁ 1-9 በበለዓም ክፉ ምክር ተሰናክለው እስራኤላውያን ከሞዓብ ሴቶች ልጆች ጋር ስላመነዘሩና በአማልክቶቻቸው ስለሰገዱ **እግዚአብሔር** በዚህ ተቆጥቶ እስራኤልን በመቅሠፍት ሲመታ እናያለን፡፡ «በመቅሠፍትም የሞተው ሃያ አራት ሺህ ነበር» (ቁ 9)፡፡

በተጨማሪ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ አሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ ለ**እግዚአብሔር** ቀንቶ ያደረገውን ድርጊት እናያለን፡፡

የስምዓን ነገድ አለቃ የነበረ አንድ እስራኤላዊ አንድ ምድያማዊትን ሴት ወደ ማኅበሩ እንዳመጣ ፊንሐስ ባየ ጊዜ ከማኅበሩ ተነስቶ በእጁ ጦር አንስቶ ወደዚያ እስራኤላዊ ድንኳን በመግባት የእስራኤላዊውንና የሴቲቱን ሆድ ወግቶ ገደላቸው፡፡ፊንሐስ ይህንን ባደረገ ጊዜ መቅሠፍቱ ከእስራኤል ልጆች ተከለከለ (ቁ 8)፡፡

ከቁ.10-13 ፡- **እግዚአብሔር** በፊንሐስ ደስ እንደተሰኘና የዘላለምን የሰላም ቃል ኪዳን እንደሰጠው እናያለን፡፡ «...ፊንሐስ በቅንዓቴ በመካከላቸው ቀንቶአልና ቁጣዬን ከእስራኤል ልጆች መለሰ...ስለዚህ የሰላሜን ቃል ኪዳን እሰጠዋለሁ፡፡ ለአምላኩ ቀንቶአልና ለእስራኤልም ልጆች አስተሰርዮአልና ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ለዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን ይሆንለታል (ቁ.11-13)፡፡

**እኛስ የምንቀናው በእግዚአብሔር ቅንዓት ነው ወይስ በራሳችን? ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለስማችን፣ ለክብራችን፣ ለወጋችን፣ ለሥርዓታችን፣ ለሃይማኖታችን መቅናት እንችላለን፡፡ ጳውሎስ**

ለሃይማኖቱ ቀንቶ ክርስቲያኖችን ያሳድድ እንደነበረ በሐዋ ሥራ 9 ላይ እናያለን። ለራሳችን የምንቀናው ቅንዓት ወይም ያለ እውቀት የምንቀናው ቅንዓት (ሮሜ 10÷2)፡፡ የእግዚአብሔርን ቤት አይሠራም እንደውም ያፈርሳል። አጉል ቅንአት ነው። «የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና» (ያዕ. 1÷20) ነገር ግን ፊንሐስ የቀናው በእግዚአብሔር ቅንአት ነበረ። የእግዚብሔር ቁጣ በውስጡ ገንፍሎ ወጣ እንጂ የራሱ ቁጣ አልነበረም።

## 2. አዲሱ የሕዝብ ቆጠራ፡ - ዘኍ. 26-27

የአሮጌው ሕዝብ ቆጠራ ብዛት 603,550 ነበረ
የአዲሱ ሕዝብ ቆጠራ ብዛት 601,730 ነበረ

(ቁ. 64-65) ከአርባ ዓመታት በኋላ አሮጌው ትውልድ በሙሉ አልቆ (ከኢያሱና ካሌብ በስተቀር) አዲሱ ትውልድ በተመሳሳይ ብዛት የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ሲዘጋጅ እናያለን።

እንደ ቀድሞው የሕዝብ ቆጠራ 12ቱ ወገኖች ለብቻቸው (ከሃያ አመት በላይ የሆናቸው) የሌዊ ወገን ደግሞ ለብቻቸው (ከአንድ ወር በላይ የሆናቸው) ነበረ የተቆጠሩት የ12ቱ ወገኖች ቆጠራ ለሰልፍ ሲሆን የሌዊ ወገን ግን ለአገልግሎት (ለመገናኛው ድንኳን) ነበረ።

አንዳንዶቹ ነገዶች (ከመጀመሪያው ቆጠራ) በቁጥር የጨመሩ ሲሆን አንዳንዳቹ ግን በጥቂቱ ወይም በብዛት ቀንሰው ነበረ። ለምሳሌ የስምዖን ነገድ በመጀመሪያው ቆጠራ 59,300 (ዘኍ. 1÷23) ሲሆን በአዲሱ ቆጠራ ግን 22,200 (ዘኍ. 26፣14) ብቻ ነበሩ። ይህም የ63% ቅናሽ ነበረ። ይህ የቁጥር ማነስ (በምዕ. 25) ላይ ካለው መቅሠፍት የተነሣ ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም ፊንሐስ የገደለው እስራኤላዊ የስምዖን ነገድ አለቃ ስለነበረ (ምዕ. 25፣14) ከሞዓብ ሴቶች ጋር ካመነዘሩት አብዛኞዎቹ ከስምዖን ነገደ ሳይሆኑ አይቀሩም። ነገር ከላይ ሲበላሽ ከታች ያሉትም ብዙ ጊዜ በዚያ መጥፎ አርአያ ስለሚወሰዱ ከስምዖን ነገድ አብዛኛዎች በዚህ መቅሠፍት ያለቁ ይመስላል።

12ቱ ነገዶች ርስት የሚሰጣቸው በቁጥራቸው መጠን ስለነበረ (ምዕ. 26÷52-54) በአመጻቸው ምክንያት በመቅሠፍት ያለቁ (የተቀነሱ) ነገዶች፤ የቁጥራቸው ማነስ ብቻ ሳይሆን ርስታቸውም ያን ያህል ያንስባቸዋል ማለት ነው።

ቁ. 64-65 «ነገር ግን ሙሴና አሮን በሲና ምድረ በዳ የእስራኤልን ልጆች በቈጠሩአቸው ጊዜ ከነበሩት ከእነዚያ መካከል አንድም ሰው አልነበረም ... ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ ከነዌም ልጅ ከኢያሱ በቀር ከእነርሱ አንድ ሰው ስንኳ አልቀረም።»

ዘኍ. 27፡ -

ሀ. ከምናሴ ወገን ስለሆኑ 5 ሴቶች ልጆች ታሪክ፣

ከምናሴ ወገን የሆነ የማኪር ልጅ የገለዓድ ልጅ፣ የኦፌር ልጅ ሰለጰዓድ ወንድ ልጅ ስላልነበረው፣ አምስቱ ሴት ልጆቹ ወደ መገናኛው ድንኳን መጥተው በማኅበሩ ሁሉና በአለቆቹ ፊት ለሙሴ «ወንድ ልጅስ ባይኖረው የአባታችን ስም ለምን ይጠፋል? በአባታችን ወንድሞች መካከል ርስትን ስጠን» ብለው ይጠይቃሉ (ቁ. 4)።

«ሙሴም ነገራቸውን በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ» (ቁ. 5)። «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው የሰለጰዓድ ልጆች እውነት ተናግረዋል በአባታቸው ወንድሞች መካከል የርስት ድርሻ ስጣቸው የአባታቸውን ርስት ለእነርሱ አሳልፈህ ስጥ» (ቁ. 6-7)።

* እነዚህ አምስት ሴቶች እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ ጥያቄ ነበረ ያቀረቡት። በእስራኤል ባህል ርስት የሚሄደው ለወንድ ልጅ ስለነበረ፣ ሴት ልጅ እንደ ወንድ ርስት የመውረስ እኩል መብት የላትም ነበር። እነዚህ አምስት እህትማማቾች በወቅቱ የነበረውን የባህል ተጽዕኖ ሳይፈሩ፣ በይሉኝታና በሁኔታዎች ሳይታሠሩ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን መብት የጎሊናቸውን ድምጽ በመስማት ሲያስከብሩ እናያለን። በእነርሱ የእምነት እርምጃ ለወደፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚገኙ ሴቶች ሁሉ አዲስ ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሰጣል (ቁ. 8-11)። እነዚህ አምስት ሴቶች በዘኍልቍ ውስጥ ሦስት ጊዜ ስማቸው ሲጠቀስ እናነባለን (ዘኍ. 26÷33፣ 27÷1፤ 36÷11)። ብዙ ጊዜ የእሥራኤላውያን ትውልድ ሲጠቀስ የሴቶች ስም አይጠቀስም (የዘሩ ሐረግ ወንዶቹን ብቻ ነው የሚቆጥረው) ነገር ግን እነዚህን ሴቶች ሦስት ጊዜ በስማቸው ይጠቅሳቸዋል።

ለ. ሙሴ እንደ አሮን ወደ ወገኖቹ እንዲከማች፣ በእርሱ ፈንታ ኢያሱን እንዲተካ ይታዘዛል።

እግዚአብሔር ሙሴን «ወደ ዓባሪም ተራራ ውጣ ለእስራኤልም ልጆች የሰጠኋትን ምድር እይ ባየሃትም ጊዜ ወንድምህ አሮን እንደ ተከማቸ

አንተ ደግሞ ወደ ወገንህ ትከማቻለህ... በቃሌ ላይ አምጻችኋልና በእነርሱም ፊት በውኃው ዘንድ አልቀደሳችሁኝምና» (ከቁ. 12-14) ይለዋል። መቀደስ የሚለው ቃል «መለየት» ወይም የተለየ ማድረግ ማለት እንደመሆኑ መጠን፤ «አልቀደሳችሁኝምና» ሲል ብትታዘዙኝ ኖሮ እኔ ከአማልክት ሁሉ የተለየሁ የአማልክት አምላክ መሆኔን እስራኤላውያን የሚያዩበት ሁኔታ ይሆን ነበረ ማለቱ ነው።

ከቁ. 15-23 ሙሴ እግዚአብሔርን፣ ከእርሱ በኋላ ሕዝቡን የሚመራ (በሕዝቡ ፊት የሚወጣና የሚገባ) ሰው እንዲሾም ይለምናል፤ እግዚአብሔርም ኢያሱን ይሾመዋል። አንድ አገልጋይ አገልግሎቱን ፈጸመ የሚባለው እርሱን የሚተካ ሰው ኮትኩቶ ሲያዘጋጅና ሲተካ ነው። ለ40 ዓመታት ሙሴ ኢያሱን ኮትኩቶታል። (በኢያሱ 1÷1) የእግዚአብሔር ቃል ኢያሱን «የሙሴ አገልጋይ» ነው የሚለው። ሙሴ በምሳሌነት ኢያሱ ደግሞ በታማኝነት በመታዘዝ እንደ አባትና ልጅ፣ እንደ መምህርና ደቀመዝሙር አርባውን ዓመት አብረው ነበሩ። እግዚአብሔር ሙሴን «የእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲታዘዙት ከክብርህ አኑርበት።» ይለዋል። አንድ የእግዚአብሔር ሰው፣ ታዳጊ አገልጋዮችን፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ ያለውን ዓላማ አስተውሎ፣ ማክበርና ለሎችም አክብረው እንዲቀበሏቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት።

## 3. ለአዲሱ ትውልድ የተሰጠው ትእዛዝ

(ምዕ. 28-36)

ይህ ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ አዲስ ባይሆንም የመጀመሪያው ትእዛዝ ለአባቶቻቸው ሲሰጥ ሳልነበሩ ለአዲሱ ትውልድ የተሰጠ ትእዛዝ ነው።

ምዕ. 28ና 29፣ ለእግዚአብሔር መቅረብ ስላለባቸው መሥዋዕቶች ይናገራል። እነዚህ መሥዋዕቶች ወቅታዊ ወይም በጊዜው የተመደቡ ናቸው።

ሀ. <u>ዕለት ዕለት የሚቀርብ መሥዋዕት</u> (ምዕ. 28፣1-8) የሚቀርበው <u>በጠዋትና በማታ</u> ነው።

«በእሳት ለእግዚአብሔር የምታቀርቡት ቁርባን ይህ ነው ለዘወትር ለሚቃጠል መሥዋዕት ነውር የሌለባቸውን ሁለት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች ዕለት ዕለት ታቀርባላችሁ አንዱን ጠቦት በማለዳ ሌላውን ጠቦት በማታ አቅርብ» (ቁ. 3)።

- አብሮ የሚሄድ የእህልና የመጠጥም ቁርባን አለ (በዘጸ. 29፥38-42 ላይ ተጠቅሶአል)።

ለ. <u>የሰንበት መሥዋዕት</u> (<u>ምዕ 28፥9-10</u>)

- ሁለት ነውር የሌለባቸው የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች፣ የእህልና የመጠጥም ቁርባን አለ።
- ይህ የሰንበት መሥዋዕት ዕለት ዕለት ከሚቀርበው መሥዋዕት በተጨማሪ በሰንበት ዕለት የሚቀርብ ነው (ቁ. 10)።

ሐ. <u>በየወሩ መባቻ የሚቀርብ መሥዋዕት</u> (ምዕ. 28፥11-15)
(ለሚቃጠል መሥዋዕት)

- ሁለት ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ
- ነውርም የሌለባቸው ሰባት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች
- አብሮት የሚሄድ የእህልና የመጠጥ ቁርባን።
- ይህ መሥዋዕት «በዘወትር (በየዕለቱ) ከሚቃጠለው መሥዋዕትና ከመጠጡ ቁርባን ሌላ ይቀርባል።»

በተጨማሪም አንድ አውራ ፍየል ለኃጢአት መሥዋዕት ይቀርባል (ቁ. 15)።

መ. <u>ለፋሲካ በዓል የሚቀርብ መሥዋዕት</u> (ምዕ. 28፥16-25)

በመጀመሪያው ወር ከአሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ <u>ለሰባት ቀናት</u> በተከታታይ በየዕለቱ የሚከተሉት መሥዋዕቶች ይቀርባሉ፤

- ለሚቃጠል መሥዋዕት ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግ፣ ሰባት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች፣ የእህል ቁርባን።
- ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል።

እነዚህ መሥዋዕቶች በዘወትር (በየዕለቱ) ከሚቀርበው ምሥኤ፥ጥ ብትጨማሪ በፋሲካ ሳምንት የሚቀርቡ ናቸው።

ሠ. በበዓለ ሃምሳ በዓል የሚቀርቡ መሥዋዕቶች (ምዕ 28፥26-31)
(በየዕለቱ ከሚቀርበው ሌላ)

- ለሚቃጠል መሥዋዕት ሁለት ወይፈኖች አንድ አውራ በግ ሰባት የአንድ አመት የበግ ጠቦቶች የእህል ቁርባን

. ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆን አንድ አውራ ፍየል፡፡

ረ. <u>በመለከት ቀን በዓል (በሰባተኛው ወር መባቻ)</u> ምዕ፡ 29፥1-6

የሚያርፈው በወሩ መባቻ ላይ ቢሆንም ለወር መባቻ በምዕ 28፥11-15 ከተጠቀሰው መሥዋዕትና ዕለት ዕለት ከሚቀርበው መሥዋዕት በተጨማሪ የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፡፡

ለሚቃጠል መሥዋዕት

- አንድ ወይፈን አንድ አውራ በግ ሰባት የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች የእህል ቁርባን

ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፡፡

ሰ. የማስተሰሪያ ዕለት መሥዋዕት (ምዕ፡ 29፥7-11)

ይህ በዓል በሰባተኛው ወር በአሥረኛው ቀን የሚውለው ብዓል ነው

- ለሚቃጠል መሥዋዕት
- አንድ ወይፈን አንድ አውራ በግ ሰባት የአንድ ዓመት የበግ ጠቦቶች የእህል ቁርባን
- ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል፡፡

**ይህ የኃጢአት መሥዋዕት በዘሌ. 16 ላይ ከታዘዘው የኃጢአት መሥዋዕትና ዕለት ዕለት ከሚቀርበው መሥዋዕት በተጨማሪ የሚቀርብ ነው፡፡**

ቁ. 11፣... **ከሚያስተሰርየው ከኃጢአት መሥዋዕት በዘወትርም ከሚቃጠለው መሥዋዕትና ከእህሉ ቁርባን ከመጠጥ ቁርባናቸውም ሌላ አቅርቡት፡፡»**

ሸ. <u>**በዳስ በዓል የሚቀርብ መሥዋዕት**</u> (ምዕ. 29፣12-38)

**ይህ በዓል ሰባት ቀናት የሚፈጅ በዓል ስለሆነ በየቀኑ የሚቀርቡ መሥዋዕቶች አሉ፡፡**

➢ **በበዓሉ በመጀመሪያው ቀን**

- 13 **ወይፈኖች፣** 2 **አውራ በጎች፣** 14 **የአንድ ዓመት ተባት የበግ ጠቦቶች፣ የእህል ቁርባን**

- ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ ፍየል

➢ በሁለተኛው ቀን

- 12 ወይፈኖች፣ የቀረው እንደ መጀመሪያው ቀን

➢ በሦስተኛው ቀን

- 11 ወይፈኖች፣ የቀረው እንደ መጀመሪያው ቀን

➢ በአራተኛው ቀን

- 10 ወይፈኖች የቀረው እንደ መጀመሪያው ቀን

➢ በአምስተኛው ቀን-

- 9 ወይፈኖች፤ የቀረው እንደ መጀመሪያው ቀን

➢ በስድስተኛው ቀን-

- 8 ወይፈኖች፤ የቀረው እንደ መጀመሪያው ቀን

➢ በሰባተኛው ቀን-

- 7 ወይፈኖች፤ የቀረው እንደ መጀመሪያው ቀን

➢ በስምንተኛ ቀን (በበዓላቱ ቀናት ማግስት)

- አንድ ወይፈን፣ አንድ አውራ በግ፣ ሰባት የአንድ ዓመት ጠቦቶች፣ የእህል ቁርባን
- ለኃጢአት መሥዋዕት አንድ አውራ ፍየል

ከላይ ያሉት መሥዋዕቶች በሙሉ «ዘወትር ከሚቀርቡት (በየዕለቱ ከሚቀርቡት) መሥዋዕቶች» በተጨማሪ የሚቀርቡ ናቸው።

በመጨረሻም ላይ: -

«እነዚህንም ከስእለታችሁና በፈቃዳችሁ ከምታመጡት ሌላ ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእህልም ለመጠጥም ቁርባን ለደኅንነትም መሥዋዕታችሁ በበዓላችሁ ጊዜ ለእግዚአብሔር አቅርቡ» ይላቸዋል (ቁ. 40)።

በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች (ዘኍ. 28 እና 29) ለእግዚአብሔር በየዕለቱና በየበዓላቱ የምሥጋናና የአምልኮ መሥዋዕት ማቅረብ እንዳለብን እናስተውላለን።

በመዝ. 49÷(50)፤ 1-14 እግዚአብሔር በእሳት ከሚቃጠል መሥዋዕት ይልቅ የምሥጋናን መሥዋዕት እንደሚፈልግ ይነግረናል።

«... ስለ ቁርባን የምዘልፍህ አይደለሁም፤
የፍየሉንስ ደም እጠጣለሁን?...
ለእግዚአብሔር የምሥጋናን መሥዋዕት ሠዋ
ለልዑልም ስእለትህን ስጥ።»

ዳዊት የእውነተኛ አምልኮና ምሥጋና ምስጢር በደንብ የገባው ሰው ስለነበረ እንዲህ ይላል፤

«የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አመሰግናለሁ፤
በምሥጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ።
ቀንድና ጥፍር ካበቀለ ከእምቦሳ ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል» (መዝ. 68÷(69)30-31)።

<u>ዘኍ. 30 ስእለትን ስለመፈጸም</u>

«ሰው ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል ወይም ራሱን በመሐላ ቢያስር፣ <u>ቃሉን አይስበር፣ ከአፉ እንደ ወጣው ሁሉ ያድርግ» (ቁ. 2)። ቃላችንን ምን ያህል መጠበቅ እንዳለብን ያሳስበናል</u>። እግዚአብሔር ስለ ቃሉ ሲናገር፤ «እፈጽመው ዘንድ <u>በቃሌ እተጋለሁ</u>፤»(ኤር. 1÷12) ።እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ወይም አደርጋለሁ ያለውን ለመፈጸም እንደሚተጋ እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን የእርሱን ባህሪይ መከተል አለብን።

በዚህ በስእለትና በመሐላ ውስጥ ግን አንዳንድ ተጨማሪ መመሪያዎችን ይሰጣል፡ - አንድ በአባትዋ ጥላ ሥር ያለች ሴት ብትሳል፣ ስእለትዋንም አባትዋ ሰምቶ ቢከለክላት ከተሳለችው ስእለት ነፃ እንደምትሆን ይናገራል፤ እንዲሁም አንድ ሴት ስእለት ብትሳል ባልዋም ሰምቶ ቢከለክላት እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላት ይናገራል።

ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ ለእግዚአብሔር ስእለት አቀርባለሁ ብለን በእግዚአብሔር ስም፣ እግዚአብሔር «አባትህንና እናትህን አክብር» «ሚስት ባልዋን ትፍራ (የአክብሮት ፍርሃት)» ብሎ ያዘዘውን የእግዚአብሔርን ቃል መተላለፍ እንደማንችል ነው። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በእኛ ላይ በምድር የሾማቸውን ሰዎች ሳንታዘዝ በሰማይ ያለውን የማናየውን እግዚአብሔርን እታዘዛለሁ ማለት አንችልም። የእነዚህ ሰዎች ትእዛዝ ከእግዚአብሔር የሚለየን እስካልሆነ ድረስ እነርሱን የመታዘዝ ግዴታ አለብን።

## <u>ዘኍ. 31 እሥራኤላውያን ምድያማውንን ሲበቀሉ፡ -</u>

እግዚአብሔር ሙሴን ምድያማውያንን ተበቀል ብሎ ያዘዋል። እሥራኤላውያንም በምድያማውያን ላይ ሰልፍ ወጥተው ወንዱን ሁሉ ይገድላሉ። በለዓምንም በሰይፍ ይገድላሉ (ቁ. 8)።

በቁ. 15 ላይ ሙሴ የምድያምን ሴቶች በህይወት ስላተረፉአቸው ይቆጣል፡ - «በውኑ ሴቶቹን ሁሉ አዳናችኋቸውን? እነሆ እነዚህ በፌጎር ምክንያት በበለዓም ምክር እግዚአብሔርን ይበድሉ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ዕንቅፋት ሆኑ» ስለዚህም በእግዚአብሔር ማኅበር ላይ መቅሠፍት ሆነ» በማለት (በዘኍ. 25) ላይ በእነዚህ ሴቶች ምክንያት በእስራኤል መካከል ስለደረሰው መቅሠፍት ይናገራቸዋል። ስለዚህ ከልጆቹ ወንዶቹን ሁሉ ግደሉ፤ (ምክንያቱም ወንድ ካደገ በኋላ የቤተሰቡንና የዘመዶቹን ገዳይ መበቀሉ አይቀርም) ወንድንም በመኝታ የሚያውቁትን ሴቶች ሁሉ ግደሉ ይላቸዋል።

ከቁ. 25-31 ስላገኙት ምርኮ አከፋፈል እግዚአብሔር ይነግራቸዋል። «ምርኮውንም በተዋጉትና ወደ ሰልፍ በወጡት <u>በማኅበሩም ሁሉ መካከል</u> አስተካክለህ ክፈል» ምርኮውን የሚካፈሉ የተዋጉት ብቻ ሳይሆኑ ማኅበሩ ሁሉ ናቸው። በክርስቶስ ኢየሱስ አካል ውስጥም የአንዱ ድል የሁላችንም ድል ነው። የአንዱ ምርኮ የሁላችንም ምርኮ ነው። «አንድ ብልት ቢሰቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ አንድ ብልትም ቢከብር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል»( 1ቆሮ. 12÷26)።

ምርኮውን የተካፈሉት ማኅበሩ ሁሉ ሲሆኑ፣ በተለይ እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ ካህናትና ለሌዋውያንም እንደ ተሰጣቸው እናያለን (ቁ. 28-30)።

ለሰልፍ ከወጡት 12,000 እስራኤላውያን አንድ ሰው እንኳን አልሞተባቸውም። እግዚአብሔር ራሱ ተበቀሉ ብሎ ያዘዛቸው ውጊያ ስለነበር ጠላትን ሁሉ (መቶ በመቶ) ደምስሰው እነርሱ ግን አንድ ነፍስ እንኳን አልጐደለባቸውም። ይህ ውጊያ እግዚአብሔር በሉቃ. 10፣19 ላይ ለእኛ ከሰጠው ሥልጣን ጋር ይመሳሰላል። «እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፤ በጠላትም ኃይል <u>ሁሉ</u> ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ፤ <u>የሚጎዳችሁም ምንም</u> የለም።»ጠላትን ሁሉ አጠፉ እነርሱ ግን <u>ምንም</u> አልተጎዱም።

በቁ. 50 ላይ ለሰልፍ ወጥተው ወርቅና ብር፣ ወዘተ ... ምርኮ ከማረኩት ውስጥ «ለነፍሳችን በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰርይልን ዘንድ ለእግዚብሔር መባ አምጥተናል» አሉ፡፡ ያገኙት የብርና የወርቅ ምርኮ የነፍሳቸውን ነገር ችላ እንዲሉ አላደረጋቸውም፡፡ የቀድሞ አባቶቻቸው ግን (የቀድሞው ትውልድ) ሥጋን ካልበላን ብለው እግዚአብሔርን ነዝንዘው ሥጋን እንደሰጣቸው፣ ነፍሳቸው ግን እንደከሳች የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (መዝ. 105 ፣(106) 14-15)፡፡

ምዕ. 32፡ - የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ከደርዳኖስ ወንዝ ወዲህ ማዶ ርስትን እንደወረሱ፡፡

እነዚህ ወገኖች፤ ርስትን ከወረስን በኋላ ዮርዳኖስን ተሻግረን ወንድሞቻችን ርስታቸውን እስኪያገኙ ድረስ በእስራኤል ልጆች ፊት እንሄዳለን በማለት ለሙሴ ቃል ይገቡለታል )ቁ. 17)፡፡ በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕ. 1፡12-18 ላይ ኢያሱ ይህንን የገቡትን ቃል ከዳን ያስተውሳቸውና እነርሱም ቃላቸውን እንደሚጠብቁ ያረጋግጡለታል፡፡ እኛም በክርስትና ሕይወታችን በክርስቶስ የሚገኘውን ሰማያዊ ርስታችንን ከወረስን በኋላ ሌሎች ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን «በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ» ለእነርሱ መዋጋት አለብን፡፡ (ቆላ. 1፣12፤ ሐዋ. 26፣17-18፤ ኤፌ. 1፣17-19)

ምዕ. 33፡ - እሥራኤላውያን ከግብጽ ጀምረው 40ውን ዓመታት ሙሉ የዞሩበትን ጉዞ በቅደም ተከተል ያሳያል፡፡

ከቁ. 1-36 እሥራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው እስከ ቃዴስ በርኔ የተጉዋዙበትን የሁለት ዓመት ጉዞ ከዘረዘረ በኋላ፤ በቁ. 37 ላይ ከቃዴስ እስከ ሖር ተራራ የነበረውን ጉዞ ይጠቅሳል፡፡ ቃዴስ በርኔ፣ እስራ ሁለቱ ሰላዮች ተልከው አሥሩ ክፉ ዜና ያመጡበትና እግዚአብሔር ያቺን ትውልድ ተቆጥቶ 40 ዓመት ትቅበዘበዛላችሁ ያለበት ቦታ ነው፡፡ ይህ የሆነው ከግብጽ ከወጡ በሁለተኛው ዓመት ነው፡ «ከቃዴስም ተጉዘው በኤዶምያስ ምድር ዳርቻ ባለው በሖር ተራራ ሰፈሩ» ይላል፡፡ የሖር ተራራ፣ አሮን በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሞተበት ተራራ ነው፡፡ አሮን የሞተው እሥራኤላውያን ከግብጽ በወጡ በ40 ዓመታቸው ነው (ቁ. 38)፡፡




አሮን፤ ከግብጽ ከወጡ በ40ኛው ዓመት እንደሞተ በቁ. 38 እናያለን፤ በዘዳ. 2፤13-14 ላይ ደግሞ ከቃዴስ በርኔ የተጓዝንበት ዘመን ሠላሳ ስምንት ዓመት ሆነ ይህም እግዚአብሔር እንደማለባቸው የቀድሞው ትውልድ እስኪጠፋ ድረስ ነው ይላል፡፡ ከ40 ላይ 38ትን ስንቀነስ ከግብጽ ከወጡ በኋላ እስከ ቃዴስ ድረስ ሁለት ዓመታት እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡ በተጨማሪም በዘኍ. 10÷11 «በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በሃያኛው ቀን» በማለት ወደ ቃዴስ ከመድረሳቸው በፊት ስለነበራቸው ጉዞ ይናገራል፡፡

በዘኍ. ምዕ. 33÷37 ላይ የ38 ዓመቱን መቅበዝበዝ በአንድ ጥቅስ መዝጋቱ ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ትኩረትና ዋጋ ያለው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነን እግዚአብሔርን በመታዘዝና ለእግዚአብሔር በመገዛት የምናሳልፈው ዘመን ብቻ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የምናባክነው ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር መዝገብ ውስጥ ምንም ዋጋ የለውም፡፡

አዲሱ ትውልድ (ከአሮን ሞት በኋላ) የሄደበትን ፈለግ ከቁ. 40-49 እናነባለን፡፡ ከቁ. 50-56 እግዚአብሔር ሙሴን፤ እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ በምድሪቱ ላይ ባሉት ሰዎችና በጣዖቶቻቸው ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይነግረዋል፡፡ «የአገሩን ሰዎች ሁሉ አሳድዱ፣ የተቀረጹትንም ድንጋዮቻቸውን ሁሉ ታጠፉላችሁ... ምድሪቱን ትወርሳላችሁ፣ ትቀመጡባታላችሁ» ይላቸዋል፡፡ ይህንን ትእዛዝ ባይፈጽሙ ግን የሚደርስባቸውን ያስጠነቅቃቸዋል፡፡

«የአገሩንም ሰዎች ከፊታችሁ ባታሳድዱ ያስቀራችኋቸው፣ ለዓይናችሁ እንደ እሾህ ለጎናችሁም እንደሚወጋ ነገር ይሆኑባችኋል፣ በምትቀመጡበትም ምድር ያስጨንቁአችኋል፡፡ እኔም በእነርሱ አደርገው ዘንድ ያሰብሁትን በእናንተ አደርግባችኋለሁ» (ቁ..55)፡፡ ለእኛም ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደ እሾህ የሆነ ነገር ካለና ካልተነቀለ ሕይወታችንን ያንቃል (ማቴ. 13÷22፤ ጢሞ. 2÷21፤ ዕብ. 12÷1-2)፡፡

ምዕ. 34፤ የሚወርሷት ርስት ዳር ድንበር

ከቁ. 1-15፣ በደቡብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና በምሥራቅ ያለውን ዳርቻ ሲናገር፣ ከቁ. 16-29 ደግሞ ምድሪቱን ርስት አድርገው የሚከፋፍሏቸው ሰዎች ከየነገዱ እነማን እንደሆኑ ይነግራቸዋል።

እኛም በአዲስ ኪዳን ያለን አማኞች የርስታችንን ዳር ድንበር ማወቅ አለብን። ይህንንም የምናውቀው 1ኛ. የተሰጠንን የጸጋ ስጦታ ጠንቅቀን ስናውቅ 2ኛ. እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ እንድናከናውንለት የሚፈልገውና የተጠራንበት ጥሪ ምን እንደሆነ ስናውቅ ነው። እነዚህንም ነገሮች የምናውቀው በኤፌ. 1÷17-18 እንደተጠቀሰው የልባችን ዓይኖች ሲበሩ ነው። በዚያን ጊዜ፤

1. የመጥራቱ ተስፋ ምን እንደሆነ
2. በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ
3. የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ እናውቃለን።

በእሥራኤላውያን መካከል ርስትን ለሕዝቡ የሚያከፋፍሉ እንደነበሩ ሁሉ በአዲስ ኪዳንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጣቸው ሰዎች አሉ፤ እነርሱንም በኤፌ. 4÷11-13 እናገኛቸዋለን። እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን፣ 1 ሐዋርያትን 2.ነቢያትን 3.ወንጌላውያንን 4. እረኞችን 5. አስተማሪዎችን የሰጠበት ምክንያት፤ «የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው። እንዲሁም ... (በክርስቶስ) ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው» (ኤፌ. 4÷12-13 በ1980 ዓ.ም. እትም)።:: ይህም ማለት እያንዳንዱ ምእመን የተጠራበት ተስፋ ምን እንደሆነ፣ በቅዱሳንም ዘንድ ያለው ርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ፣ የኃይሉም (የእግዚአብሔር ኃይል) ታላቅነት ምን እንደሆነ ተረድቶ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መንፈሳዊ ርስት መውረስ እንዲችል ለማድረግ ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ቅዱሳን (አማኞች) ቦታቸውን (ርስታቸውን) አውቀው እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ያለውን ጥሪና አገልግሎት እንዲፈጽሙ ለማድረግ ነው። በሐዋ. 26÷17-18 እግዚአብሔር ለጳውሎስ «የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ

አድንሃለሁ» በማለት ያልጻኑ የወንጌልን ቃል ሰምተው በማመን የኃጢአትን ስርየት እንዲያገኙ አማኞች ደግሞ በተቀደሱት መካከል ርስትን እንዲያገኙ መንፈሳዊ ዓይናቸውን እንዲከፍት ያዘዋል:: የእግዚአብሔርን ቃል ስንመለከት ጳውሎስ በኤፌ. 4 ላይ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ከሰጠው አምስት ስጦታዎች ውስጥ በሦስቱ ያገለግል እንደነበረ እንረዳለን:: ሐዋርያ፣ ወንጌልን ሰባኪና አስተማሪ ነበረ (1ጢሞ. 2÷7፤ ሐዋ. 13÷1-3፤ ሐዋ. 20÷24)::

በሕዝ. 47÷13-20 እስራኤላውያን በኢያሱ ዘመን የወረሱትን ርስት በኃጢአታቸው ምክንያት ካጡና ከተሰደዱ በኋላ፣ እንደገና ከስደት ተመልሰው የሚወርሱትን ዳር ድንበር ይዘረዝራል:: ዳር ድንበሩም ከዘኍልቁ ምዕራፍ 34 ጋር ተመሳሳይ ነው::

## ዘኍ. 35 ለሌዋውያን የተሰጡ ከተሞች

እነዚህ ከተሞች በአጠቃላይ 48 ከተሞች ሲሆኑ ስድስቱ የመማጸኛ ከተሞች ናቸው (ቁ. 6):: እነዚህ የመማጸኛ ከተሞች አንድ ሰው በስህተት ነፍስ ከገደለ ሄዶ የሚሸሸግባቸው ከተሞች ናቸው:: «በስሕተት ነፍስ የገደለ ወደዚያ ይሸሽ ዘንድ የመማጸኛ ከተሞች እንዲሆኑላችሁ ከተሞችን ለእናንተ ለዩ:: ነፍሰ ገዳዩ በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ እንዳይሞት ከተሞቹ ከደም ተበቃይ የመማጸኛ ከተሞች ይሁኑላችሁ» (ቁ. 11-12)::

አውቆ የገደለ ግን ፈጽሞ ይገደል (ቁ. 16-21):: ድንገት ሳያውቅ በአደጋ ምክንያት ሰው በእጁ የሚሞትበት ሰው ግን ወደ መማጸኛ ከተማ ሄዶ መሸሸግ ይችላል::

«ማኅበሩም ነፍሰ ገዳዩን ከደም ተበቃዩ እጅ ያድነዋል» (ቁ. 25)::

«ነፍሰ ገዳዩ ግን ከሸሸበት ከመማጸኛው ከተማ ዳርቻ ቢወጣ ደም ተበቃዩም ከመማጸኛው ከተማ ዳርቻ ውጭ ቢያገኘው ደም ተበቃዩም ነፍሰ ገዳዩን ቢገድለው የደም ዕዳ አይሆንበትም ዋነኛው ካህን እስኪሞት ድረስ በመማጸኛው ከተማ ውስጥ መቀመጥ ይገባው ነበርና» (ቁ. 26)::

በዚህ ዘመን ያለን የመማጸኛ ከተማ (ጠበቃ) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: «ልጆች ሆይ፣ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ:: ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»

(1ዮሐ. 2÷1)፡፡ «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል... በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» (1ዮሐ. 1÷7-9)፡፡

በአዲስ ኪዳን፣ ጥላቻ ነፍስን እንደመግደል ነው፤ «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው» (1ኛ ዮሐ. 3÷15)፡፡

«ደም ምድሪቱን ያረክሳታልና የምትኖሩበትን ምድር አታርክሱት፤ በደም አፍሳሹ ደም ካልሆነ በቀር ምድሪቱ ከፈሰሰባት ደም አትነጻም» (ዘኍ. 35÷33)፡፡ በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው ነፍስ ከገደለ ደም ካፈሰሰ የእርሱ ደም መፍሰስ ነበረበት፤ በአዲስ ኪዳን ግን ደም ላፈሰሰ ሰውም ቢሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹህ ደሙን ስላፈሰሰለት የእርሱ ደም መፍሰስ የለበትም፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመነ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያስተሰርይለታል፡፡

<u>ዘኍ. 36</u> በምዕራፍ 27 ላይ ስለተጠቀሱት የሰለጰአድ ሴቶች ልጆች ተጨማሪ ታሪክ ይናገራል፡፡ እነዚህ አምስት የሰለጰአድ ሴቶች ልጆች በምዕራፍ 27 ርስትን በአባታቸው ወንድሞች መካከል ከተቀበሉ በኋላ ከሌላ ነገድ ባልን ቢያገቡ ርስቱ ወደ ባላቸው ወገን ስለሚሄድና የምናሴ ነገድ ርስት መሆኑ ስለሚቀር እግዚአብሔር ከነገዳቸው ብቻ ባልን እንዲያገቡ ያዛቸዋል፡፡ «እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እንዲሁ የሰለጰአድ ሴቶች ልጆች አደረጉ» (ዘኍ. 36÷10)፡፡

በምዕራፍ 27 <u>መብታቸውን ሲያስከብሩ</u>፣ በምዕራፍ 36 ደግሞ <u>ግዴታቸውን ሲፈጽሙ</u> እናያለን፡፡ ጤናማ የክርስትና ሕይወት የልጅነትን መብት ማስከበር ብቻ ሳይሆን ግዴታንም መፈጸም ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት፣ ጥያቄዎች

1. አሪት ዘኍልቁ በስንት ክፍሎች ይከፈላል? ከፍሎቹስ ምን ምን ናቸው?
2. የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጻፈ በሚለው መሠረት በዚህ መጽሐፍ የምናያቸው ሁለት የእግዚአብሔር ባሕርያት ምንድን ናቸው? ለእኛስ የሚያስተላልፉት ትምህርት ምንድነው?
3. ሦስቱ የሌዋውያን ልጆች ስምና የተሰጣቸው ልዩ ልዩ ኃላፊነት ምንድን ነበረ?
4. አሥራ ሁለቱ ነገዶች (ዮሴፍ ሁለት ድርሻ ስለተሰጠው)፤ ሦስቱ ሌዋዊ ወገኖች፤ ሙሴና የአሮን ቤተሰብ ከመገናኛው ድንኳን ዙሪያ እንዴት ነበረ የሚሠፍሩት? ከዚህ ሥርዓት ምን ትማራለህ?
5. አንድ ሰው የናዝራዊነትን ስእለት ሲሳል ራሱን ከሦስት ነገሮች ይጠብቃል። እነዚህ ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው?
6. በእስራኤላውያን መካከል የሚነፉ ሁለት መለከቶች ነበሩ። እነዚህ መለከቶች የሚነፉባቸውን አራት ምክንያቶች ግለጽ?
7. ሙሴ ያንን ሁሉ ድንቅና ተአምራት ካየ በኋላ እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ለማመን የተቸገረበትን ሁኔታ ግለጽ።
8. እግዚአብሔር ሊሰጠን ያለውን ርስት ስለ መውረስ ከዘኍልቁ መጽሐፍ የምንማራቸው ነገሮች ምንድናቸው/ በአዲስ ኪዳን የምንወርሰው ርስት ምንድን ነው?
9. ሙሴና አሮን ወደ ተስፋይቱ ምድር አትገቡም የተባሉበት ምክንያት ምንድነው? እግዚአብሔር «በእሥራኤል ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ» ሲል ምን ማለቱ ነው? (ሰው እግዚአብሔርን እንዴት ይቀድሳል)?
10. ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው እባብ ከክርስቶስ ጋር ያለውን ምሳሌነት አስረዳ።
11. በለዓም የተናገራቸውን ትንቢቶች ስንመለከት ከእግዚአብሔር የመነጨ ትክክለኛ ቃሎች መሆናቸውን እናስተውላለን። እውነተኛ ትንቢትን እየተነበየ የእግዚአብሔር ቃል ለምን እብድ ነቢይና መተተኛ በማለት ያወግዘዋል?
12. አምስቱ የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች በዘኍልቁ ውስጥ በተደጋጋሚ በስማቸው ሲጠቀሱ እናያለን። ከእነርሱ ታሪክ ምን እንማራለን?